# የጌታ እራት

... በአሪዞና ከተደረጉት አስራ አምስት፡ በርካታ አገልግሎቶች የተነሣ ጉርሮዬ ይዞኛል። አስደሳች ጊዜ አሳልፈናል። ጌታ ኢየሱስ አብዝቶ፡ እና አትረፍርፎ ባረከን። በጥቂቱም ቢሆን የጌታ ስልት ለመጠቀም ሞክረው ነበር፡ እንደዚያ ብገልጸው፡ ምንም ችግር እንደማይኖር ተሰፋ አደርጋለሁ፡ በመጀመሪያ፡ ሄደን በየቦታው ቅስቀሳ-አደረግን። ቀኑ ከመድረሱ ከበርካታ ቀናት በፊት ወደዚያ ወርጄ፡ በፊኒክስ እና በዙርያዋ ሁሉ ላይ አስር ወይም አስራ ሁለት አገልግሎቶችን አካሄድኩኝ፡ በሳኒስሎፕ እና በቴፔ እና ሜሳ እና በዙርያ ባሉ ሁሉ፡ መጠነኛ ቅስቀሳ-ካደረግን በኋላ ሁሉንም ወደ አምስት ቀናት ኮንቬንሽን እንዲገኙ አደረግናቸው። ያም በሰሜን አሜሪካ ካደረግናቸው ኮንቬንሽኖች ትልቁ ነበር። እጅግ ታላቅ ነበር። እጅግ የተለየ ቁርስ፡ እ—እንዲሁም የ—የድግስ ምሽት ነበረው።

2 ሰንቶች መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ መገመት አልችልም። ብዙዎች መንፈስ ቅዱስ እስኪሞሉ ድረስ እጅግ—ልዩ ነበረ፡ ብዙዎች ተፈውሰዋል የ—የዳኑም አሉ፡ እ—እጅግ ልዩ ነው። ስለዚህ ጊዜው ሲፈጸም ስናየው እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ብዙ ታላላቅ ሰዎች መጥተዋል። አንዳንዶች...

3 ይህ ወንድም ኔቪልን በጣም ያስደሰተዋል። እዚህ አገር... ካሉት ከታላላቆቹ የፕሪስባይቴሪያን የኮሌጅ ተቋማት አንዱ የመጣ፡ አንድ የፕሬስባይቴሪያን አገልጋይ፡ በመንፈስ ሆኖ ሲያሸበሽብ አይቼዋለሁ። ኦህ፡ ማይ፡ ለየት ያለ ነገር ነበረ፡ መንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ከዚያም ነገረኝ፡ "ከቴፖችህ አንዱን ቅጂ አገኘሁ፡" አለኝ። "እምብዛም መልካም አልነበረም፡" አለኝ። እንዲህ አለ፡ "ትንሽ የመቆራረጥ ነገር ነበረው፡ ቢሆንም፡" "ወደ ኮሌጃችን ወሰጄ ከፈትኩላቸው፡" አለኝ። እንዲህ አለኝ... ሰውዬው ታላቅ የሳይኮሎጂ ሰው ስለሆነ፡ ሁሉንም ጸጥ አሰባላቸው። "ምንም ቢሆን፡ ቢያንስ፡ አንድ ጊዜ ሰምተውታል፡" አለ። በተጨማሪም ያደረገው ነገር...

4 መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ፡ በቤተክርስቲያኑ በመንፈስ እስከ ማሸብሸብ ደረሰኩ አለ። እነርሱም፡ "ሬቨረንድ ሆይ፡ አዲሱን አካሄድ የምትማረው መቼ ነው" አሉት?

5 እሱም፡ "ጉባኤዬ ይህን በሰማ ጊዜ" አላቸው። እጅግ ደስ የሚል ነገር ነው፡ እና፡ የፕሬስባይተሪያን የስልጣን ተዋረድ፡ አዎን፡ "ጉባኤዬ ይህን በሰማ ጊዜ፡" አላቸው። ስለዚህ ያ ጥሩ ነገር ነው። እንደ ህጻን ልጅ፡ አዲስ የሆነ ነገር... እንግዲህ፡ ምን ሊሆን እንደሚችል ትገምታላችሁ፡ እንግዲህ፡ በቦስተን በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በታላቁ የፕሬስባይቴሪያን ኮሌጅ፡ የስነ ልቦና ፕሮፌሰር መሆን ማለት ታውቁታላችሁ።

6 ከማዮስ የልብ ቀዶ ጥገና ሐኪሞች አንዱ ወንጌልን በመንፈስ ሲሰብክና በልሳኖች ሲናገር አይቻለሁ። ኦህ፡ ማይ! ከሰባተኛው-ቀን አድቬንቲስት የሆነ ሌላ ስፔሻሊስትም፡ እንዲሁ አይቻለሁ፡ እርሱም... የልብ እና የጉሮሮ እ—

እ—እስፔሻሊስት ነበረ፡ ሰውዬው፡ ሽማግሌ ነው፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተቀበለ። ተቀብሎታል። አንድ ቀን ምሽት አደባባዩ ላይ እጄን ጫንኩበት፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ። ስለዚህ... ጌታችን ያደረጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ እናመሰግነዋለን፡ በተለይም በዚህ ጊዜ አይተነዋል።

7 እኔም፡ "ሰነፏ ድንግል ዘይት መለመን የጀመረችበት ይህ ጊዜ የትኛው ጊዜ እንደሆነ አስተውላችሁታልን" አልኋቸው? ሙሽራው የመጣበት ጊዜ ነው፡ ህዝቡም፡ የተዘጋጁ ሁሉ ገቡ። ኦህ፡ በመጨረሻ ቀናት ውስጥ እየኖርን መሆናችንን በማወቄ በጣም ደስተኛ ነኝ። አያችሁ? አለም እስካሁን ካወቀቻቸው እጅግ በጣም አስደናቂ ጊዜያት በአንዱ ላይ እየኖርን እንደሆነ አምናለሁ፡ የምንኖረው በጌታ ምጽአት ዋዜማ ላይ ነው። አይደንቅም ወይ? እስቲ አስቡት፣ በቅርቡ ይመጣል፣ ሁሉም በሚባል ደረጃ ቅዱሳት መጻሕፍት ተፈጽመዋል! እና ስለዚህ እሱን በማንኛውም ጊዜ አሁን እንጠብቀዋለን። መኖር ያለብን በዚህ ተስፋ ውስጥ ነው፡ ምክንያቱም፡ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት ይችላል። በጸሎት እራሳችሁን አዘጋጁ፣ ተዘጋጁ!

8 ዛሬ ባደረግኳቸው አንዳንድ ንግግሮች፡ መጀመርያ፡ ከፎርሞሳ የመጣች፡ አንዲት ሚሰዮናዊት አገኘሁ፡ እጅግ ብርቱ ሴት፡ ሰባ-ሶስት ዓመቷ፡ ላለፉት አርባ-አምስት ዓመታት አልፋለች። አሁንም—ወይዘሮ ናት፡ ወጣት ሴት በነበረች ጊዜ ውብ የነበረች ይመስለኛል። ስለ አስተዳደግዋም "አዎን" ማለት አዎን ነው፡ "አይደለም" ማለት አይደለም ነው በሚባልበት የክርስቲያን ቤት ውስጥ እንዳደገች ተናግራለች። ያደገችው በእንደዚህ አይነት ጥብቅ ትምህርት ነው። እንዲህ አለችኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ገና እድሜዬ፡ ኦህ፡" እንዲህ አለች፡ "ገና የሰምንት አመት ልጅ ሆኜ፡ ሕይወቴን ለጌታ ኢየሱስ የሰጠሁ መሰሎኛ ነበር።" እንዲህ አለች፡ "የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለሁ፡ ሁለተኛውን በረከት ማግኘት አለብሽ በሚል፡ በአንድ የቤተ እምነት አገልጋይ ተታልዬ ነበር፡" "በዚያም እጅግ ተታለልኩ፡" አለች። "የአስራ ሰባት አመት ልጅ ሳለሁ ግን፡ በእውነት መንፈስ ቅዱስን ተቀበልኩኝ፡" አለች። አሁንም ከእነዚህ ሰነፎቹ የባፕቲስት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዳንዶቹን ለመቀስቀስ ወደዚህ ተመልሳለች። እሷ ራሷ ባፕቲስት ናትና፡ እንዲህ ብላለች "ሙት" አይቼአለሁ ከ—ከተባለ፡ "እነዚህ የሞቱ የባፕቲስት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡" አለች። "አስከሬኖች" ትላቸዋለች።

9 "እንግዲህ፡ ምናልባት ግንባር ላይ ስትሰለፉ... " እንዲህ ይሆናል ብዬ አሰባለሁ፡ እሷም ብትሆን... እስቲ አስቡት፡ ሃምሳ-ሁለት፡ ሆኛለሁ፡ ገና ከመወለዴ በፊት ሚሰዮናዊ ሆና ነበር። ወደ ሚሲዮናዊነት መስክ ለመሄድ በጣም አርጅቻለሁ ብዬ አስብ ነበር። ከዚያም "አቤቱ፡ ይቅር በለኝ፡ ጌታ ሆይ፡" አልኩኝ።

10 አሁንም አቅሟ፡ ንቃቷ ሁሉ፡ በጥሩ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። በመንገዷ ሰላጋጠሟት ልምምዶች፡ እና ወንጌል በፎርሞሳ፣ እና—እና በቻይና፣ እና በጃፓን እና በሌሎች ቦታዎች እንዴት እንደሚያስፈልግ ነገረችኝ። ስለዚህ አሁን ከተልእኮው አሰናብተዋታል፡ "እንግዲህ፡ ከሰባ በላይ ከሆንሽ በኋላ ወደ ሚሲዮኑ መስክ እንድትሄጂ አይፈቀድልሽም፡" አሏትና፡ መለሷት። እሷ ግን አታርፍም፡ አሁንም ወደ ባፕቲስት ሰብሰባዎች ትሄዳለች። እንደተናገረችውም፡ "ቢሊ ግራሃም፡" አለች፡ "የባፕቲስት መእልእክት የሚያስተላልፍበት መንገድ፡

የባፕቲስት ቤት ክርስቲያንን ባለዕዳ ያደርጋታል።" ስትናገርም፡ "መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉ ድረስ በቂ ርቀት አያስጉዛቸውም፡" አለች። ኧረ፡ እህት ሆይ፡ በዚያ ጸንተሽ ኑሪ። መልካም ነው። እንዲህ አለች፡ እነዚያ ቻይናውያን አለች፡ እንዲሁ ወጥተው፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን" እንዲሉ አላደርጋቸውም አለች። "ያም ቢሆን መልካም ነው፡" ቢሆንም፡ አንድ ነገር እስኪከሰት ድረስ እዚያ አቆያቸዋለሁ አለች፡ ከዚያ በኋላ እውነተኞች ክርስቲያኖች ይሆናሉ።

11 እኔም "መሆን ያለበትም እንደዚያ ነው፡ እህቴ። ንገሪያቸው፡ የሆነ ነገር እስኪከሰት ድረስ አቆያቸው፡" አልኳት።

12 ለምሣሌ ሐዋርያቱ፡ አሁን፡ ከዘጠኝ ቀን በኋላ እንዲሁ ቢሉስ፡ "አሁን እንዳገኘን እናምናለን፡ ይኸውላችሁ፡ በእምነት ብቻ እንቀበለው እና ወደ ሥራችን እንሂድ"? አያችሁ፡ በጭራሽ አይሰራም ነበር። የሆነ ነገር መከሰቱን እስኪያውቁ ድረስ እዚያ ጠበቁ። ዛሬም ችግራችን ያ ነው፡ በቂ ጊዜ አንታገስም። እንግዲህ፡ የፈለግነው አይነት ህይወት እየኖርን፡ እና የፈለግነውን እያደረግን፡ ምንም የማይመስለን ስለዚህ ነው፡ ምክንያቱም በቂ ጊዜ አንታገስም። ዛሬ ገብተን፣ ነገም እንወጣለን፣ **በዚህ** መንገድ እና **በዚያ** መንገድ። በሩን ከኋላህ ዘግተህ እስክታገኘው ድረስ ተግተህ በቂ ጊዜ ብትጠብቅ፡ ሁሌም በዚያ ትጸናለህ። እስከ ቤዛ ቀን ድረስ ትታተማለህ። በዚህ በጣም ደስ ብሎኛል።

13 እንዳልኩትም፡ በፊኒክስ እና በሸለቆው ዙርያ እና በዚያ ካሉት ብዙ ክርስቲያኖች ጋር፡ ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል፡ ብዙዎቹ ውድ ህይወታቸውን አጥብቀው ይዘዋል።

14 ያቻትና ከሚስቴ ጋር፡ አንድ ላይ፡ ወደ ደቡብ ተራራ ሄጄ ነበር። ያን ቀን፡ ከጓደኞቼ፡ ወንድሜ፡ ዶክ፡ ሁለቱን ሴቶች ጠበቀልን፡ ወንዱ ልጅ ደ—ደግሞ ወንድም እና እህት ውድ ጋር ይዘውልን፡ እኔ እና ባለቤቴ ሁለተኛ የጫጉላ ሽርሽር ሆነልን። እሷም "ቢል፡ ታውቃለህ፡ ይህ ከመጀመሪያው የጫጉላ ሽርሽር ይበልጣል፡" አለችኝ። አለችም፡ "በመጀመሪያው የጫጉላ ሽርሽር በሄድን ጊዜ፡ ብቸኛው ያደረግኩት ነገር አንተ ከአደን እስክትመጣ ድረስ ካምፑ ውስጥ ቁጭ ብዬ አንተን መጠበቅ ነበር፡" አለች።

15 ይኸውላችሁ፡ ያን ጊዜ አንድ ስልት ተጠቀምኩ። "እንግዲህ፡ ያው፡ በቂ ገንዘብ የለኝም፡" ብዬ አሰብኩ። ለአደን ጉዞ ለመሄድ፡ በዱቄት ቆርቆሮ ውስጥ ገንዘብ አጠራቅሜ ነበረ፡ ቢሆንም በዚያ መኸር ላገባ ነበር። ስለዚህ፡ "ሁለቱም አንድ ላይ ላርገው፡" ብዬ አሰብኩ። ስ—ስለዚህ ለአደን ጉዞ እየተጓዝኩ ሳለሁ፡ የጫጉላ ሽርሽርም ይሁን አልን፡ ስለዚህ፡ አንድ ላይ ተስማማን። በዚህ ጊዜ ግን ዋጋ ከፍለን የእውነት ወጣን፡ እንዲሁም፡ ይኸው፡ ጥሩ ጊዜ አሳለፍን።

16 ከተበርናክል የመጡ ብዙዎቹ በዚያ ነበሩ። ወንድም ሶትማን፡ ከኋላ ካሉት ከቤተሰቡ ጭምር፡ ወንድም ቶም ሲምፕሰን እና ሰዎቹ፡ እና ወንድም ማጊየር፡ ሁላችንም በጌታ ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል።

17 ስለዚህም ከፊኒክስ በስተደቡብ ወዳለው፡ ወደ ደቡብ ተራራ ወጣን፡ በዚያም ከጫና ሁሉ ራቅን። ኧረ! የዘመናዊው ከተማ ጫናዎች! ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ፡ ኃጢአት፡ እና ዓመፅ መግባቱ ምንም አያስደንቅም። የፊኒክስ ሸለቆ ለማየት ከዚያም ሆኜ አማትሬ አየሁ፡ ከተቀመጥንበት

ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሆኜ ተመለከትኩና፡ ባለቤቴን እንዲህ አልኳት፡ “እኔ የሚገርመኝ፡ እዚህ በተቀመጥንባት አስራ አምስት ደቂቃ ውስጥ፡ በዚያች ከተማ የእግዚአብሔር ስም በከንቱ ስንቴ ተነስቶ ይሆን? ” እህም?

18 ይህም፡ በዚያ፡ በሜትሮፖሊታን አካባቢ ያሉትን፡ እነ ቴምፔ እ—እና ስኒስሎፕን ጨምሮ፡ በዙርያ ባሉት ሁሉ፡ በሸለቆ ውስጥ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እገምታለሁ። እንዲህ አልኳት፡ “ከሦስት መቶ ዓመታት በፊት እዚህ ከቁልቋል እና ቀበሮ በስተቀር ምንም አልነበረም። ምናልባትም፡ በጌታ ዘንድ፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ የሚሻል ይመስለኛል” አልኩኝ። እውነት ነው። እርግጥ ነው የገነቧት ታ—ታላቅ ከተማ፡ እና ቤቶች እና ሁሉም ነገር፡ አስደናቂ ናቸው። ቢሆንም ወንዱም ሴቱም፡ እጆቻቸውን ከፍ አርገው በጎዳናው ላይና ታች እየወረዱ እግዚአብሔርን እያከበሩና፡ እያመሰገኑ ቢሄዱ ጥሩ ነበር። ከዚያ ይልቅ፡ ግን፡ እርግማን፡ ክፋት፡ እና መጠጥ አበዙ። ብቻ ሥልጣኔ ይግባ እንጂ፡ ክፋት አለ።

19 እንዲህ አልኩ፡ “ትላንት አመሻሽ ላይ ስንት ዝሙት ተፈጸመ፡ ትላንት ማታ በዚህች ከተማ! ስንቶች ሰከሩ! ስንት ቤቶች... ስንት—በመጨረሻው ሰዓት፡ በዚህች ታላቅ ከተማ ስንት ሥርዓት አልበኝነት ተደርጎ ይሆን!”

20 እኔ ይህን ሳስብ ሳለሁ፡ ሚስቴ እንዲህ አለችኝ፡ እንዲህ በማለት ተናገረች፡ “ታዲያ ወደዚህ መምጣት ምን ጥቅም አለው? ወደዚህ ለመምጣትስ ከቤት ለምን ወጣህ?

21 ከዚያም አልኩ፡ “ዋናው ነገሩ ይህ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ፡ እርግጥ ይህ በብዙኃኑ ዘንድ ያለ ነገር ነው፡ ይህን እንጂ በመካከላቸው ታናሽ መንጋ አለ። ትናንት ምሽት ወደ አገልግሎት ሲመጡ፡ ስንት ታማኝ ጸሎቶች ወደ ሰማይ አረጉ? ”

22 ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ እስኪሞሉ ድረስ እጅግ መልካም አደረገልን፡ ወደ ኋሮው መጠጋት እስኪሣነን ሆኖ ነበር። ድርጅቶቹ እና ሌሎቹ ሁሉ፡ ጌታም መንፈሱን አፍስሶ ሁሉንም ባረካቸው። በወንጌል ደጋግሜ መታኋቸው እንጂ፡ ቡጢ አልያዝኩባቸውም። እርግጥ ነው፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ከበድ ይላል፡ እንደሚገባኝ ብቸኛው መንገድ ያ ነው። እዚህ ጋር ከባድ ነው። ሁላችንም በምንቆምበት በፍርድ ፊትም እጅግ የከፋ ከባድ ይሆናል። ስለዚህ፡ በአጠቃላይ፡ እጅግ መልካም ነበር። ይህች ቤተክርስቲያን ስለ እኛ ስለፀለየች እና ስላሰጠጋችን፡ እ—እና ወደ መስቀሉ እንድንቀርብ ስላደረገችን ማመስገን እንፈልጋለን።

23 አሁንም ወደ ቤት ተመልሼ፡ ስለመጣሁ፡ ዛሬ ጠዋት ምናልባት ለታመሙት ለመጸለይ እነሆ ወደዚህ ወርጃለሁ። በመጠባበቅ ላይ ያሉ ብዙ ቃለመጠይቆችን ይጠብቁኛል፡ አንዳንዶቹ እዚህ ከመጣሁ ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ሁለት ቀናት የደረሱኝ ጉዳዮች፡ እንዲሁም ከሄድኩኝ ጊዜ ከአንድ ወር በፊት እየጠበቅኩኝ ያሉም አሉ። ስለዚህ በተቻለ ፍጥነት ወደ እነርሱ ለመግባት እየሞከሩ ነው፡ ከተለያዩ ቦታዎች የሰበሰቧቸው ናቸው።

24 ጌታ ቢፈቅድ፣ ከሁለት ሳምንት በኋላ፣ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ወደምትገኘው፣ ወደ ቱሰን እሄዳለሁ። አሁንም በዚህ ጊዜ፡ ስለ ቢዝነስሜኖቹ እንድትጸልዩ አሳስባለሁ... የጌታ ፈቃድ እንደሆነ ሳላምንም ምንም ማድረግ

ፈጽሞ አልወድም። ስለዚህ፡ ቀጣዩ ጉባኤ በሞዴስቶ ይደረጋል ከዚያም በዋሽንግተን፡ በዋሽንግተን፡ ግዛት፡ እና ወደ ዙሪክ፡ ከዚያም ወደ ፍልስጤም፡ ከዚያም ወደ ደቡብ አፍሪካ ይካሄዳል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ከአሁን እስከ ሰኔ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በእነዚህ ሁሉ ስብሰባዎች ላይ እንድሰብክ ተጋብዣለሁ። ምናልባት እንደገና ወደ ደቡብ አፍሪካ የመመለስ እድል ይሰጠኝ ይሆናል። እነሱ ይጠይቃሉ፡ በየወሩ ግብዣዎችን እንቀበላለን። ይህ ከሆነ...

25 በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፡ በጴንጤቆስጤ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ትልቅ መከፋፈል አለ። እና ከአንደኛው ወገን ጋር ከሄዳችሁ፡ ሌላኛው ወገን ጋር ምንም ማድረግ አይፈልግም። መተባበርም አይፈልጉም፡ በዚህም ምክንያት በልቤ እንድሄድ ጥሪ ቢኖረኝም አሁን ለአምስት ዓመታት ያህል ሳልሄድ ቆይቻለሁ። ምናልባት አሁን፡ ቢዝነስሜኖቹ ካስገቡኝ፡ ቢያንስ ግንኙነቶችን ለመመስረት ይረዳኛል፡ እነሱ የሁለቱም ቡድኖች አካል ናቸው፡ አያችሁ፡ በሁሉ ዘንድ እንዲገኙ ያደርጋቸዋል። ሁሉም መጥተው በዚህ ላይ መተባበር አለባቸው ምክንያቱም የገንዘብ ፍላጎታቸው—የቤተ ክርስቲያኖቻቸው የገንዘብ ፍላጎቶች በዚያ አለ፡ ስለዚህ ፊታቸውን ለማዳን መምጣት አለባቸው፡ አያችሁ። ስለዚህ ምናልባት የጌታ ፈቃድ ሊሆን ይችላል, ሆኖም ግን፡ አላውቅም። ጥሩ ይመስላል፡ ግን አላውቅም።

26 የዚህን አመት፡ መርኃ ግብር፡ ወይም፡ ጥሪዎችን፡ ወንድም ቦርደርስ አቅርቦልኛል። እንደ እውነቱ ከሆነ፡ በባለፈው የገና በዓል፡ ከዙርያው ሁሉ ከደረሱት ጥሪዎች ይልቅ፡ **በእጥፍ** በሚወፍር መዝገብ የተሰነደ ነው። ነገሩን ለመፍታት መሞከር ለሰው አእምሮ እጅግ ከባድ ነው፡ እስከ አሁን ድረስ ማናቸውንም አልተቀበልኩም። ዝም ብዬ ሰብሰባ አደርጋለሁ፡ ከዚያ ጌታ እንድሄድ የሚፈልገኝን ለማየት እጠባበቃለሁ፡ ከዚያም ወደሚቀጥለው ልለፍ፡ ከዚያም ወደሚቀጥለው፡ እና እንድሄድ ወደሚነግረኝ ቦታ ሁሉ እሄዳለሁ። ስለዚህ፡ ጸልዩልኝ።

27 ባለፈው አመት፡ ከአንድ ወንድም ጋር በነበርኩበት ጊዜ አስታውሳለሁ... ወይም እህት ኮክስ፡ ወንድም አርጋንብራይት ጉዞ ወደ አንኮሬጅ እንዳደርግ በጠየቀኝ ጊዜ። ደህና ነው ብዬ በግምት ወደዚያ ብሄድ ምን እሆን ነበር?

28 አሁን፡ ስለ **ግምት**፡ እያሰብኩ ነበር፡ በዚያ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሰብኬአለሁ። ወደዚያ በወጣሁ ጊዜ፡ ለቴፕ ቦይስ እንዲህ አልኳቸው፡ "የቴፕ ቅጂ እንዳታደርጉ። እዚህ የሰበኩትን አይነት ስብከት እሰብካለሁና፡ ወደ ቴፖቹም አትሂዱ።" እዚህ እንዳደረግኩት አንድ የሰብኩ ይመስለኛል፡ ሌሎቹ ሁሉ ግን አዳዲስ ነበሩ። እናም ወንድም ማጊየር፡ ሁሉንም አገኛቸው።

29 ግምት። ስለዚህ እኔ፡ ወደዚያ **በግምት** ሄጄ ብሆን ኖሮ፡ ከሆነው ነገር በተቃራኒው ይሆን ነበር፡ ራእዩ ሳይፈጸም ይቀር ነበር። ነገር ግን ራእዩ ተፈጸመ፡ ጌታ እንዴት እንደባረከን፡ ሁላችሁም ታውቃላችሁ።

30 አሁን፣ ለረጅም ጊዜ በልቤ ውስጥ የኖረ ሌላ ነገር አለ። ቤተክርስቲያን ሆይ፡ ስለዚህ ጸልዩ። ከልጅነቴ ጀምሮ በዚህ ክልል እርካታ እንደሌለኝ ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ወደ ምዕራብ ለመሄድ ሁል ጊዜ በልቤ ውስጥ ጥልቅ ፍላጎት ነበረኝ። በትንሿ ቤት ለ-አማቴ-ሣር እያጨድኩላት የነበርኩበትን ጊዜ አስታውሳለሁ ያቺ... የቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነችው፡ ትንሿ ቤት። በደረጃው

ላይ ተቀምጬ ነበር፡ መንፈስ ቅዱስም ተናገረኝ፡ "እንደ አብርሃም ሙሉ በሙሉ እስካልታዘዝከኝ ድረስ፡ ከእንግዲህ ልባርክህ አልችልም፡" አለኝ። አያችሁ? እግዚአብሔር፡ አብርሃምን፡ እንዲለይ እና ወደሱ እንዲሄድ ተናገረው። በዚያን ጊዜም፡ አባቱንና፡ የወንድሙን ልጅ፡ ከእርሱ ጋር ወሰደ። አብርሃምም አምላክን ሙሉ በሙሉ በታዘዘ ጊዜ፡ እግዚአብሔር የገባለትን የተስፋ ቃል በሙላት ተከናወነ። እዚህ ከያዙኝ፡ ቀንደኛ ማሰሪያዎች መካከል፡ አንደኛዋ ስንስለት እናቴ ነበረች። ታውቃላችሁ። አሁን ግን እናቴ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለመሆን ሄዳለች። በ—በየትኛው መንገድ መሄድ እንዳለብኝ፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡ ስለዚህ ጸልዩልኝ።

31 እንግዲህ፡ ወንድም ኔቪል፡ ወደ መድረክ ወጣሁ፡ "እሺ፡ ወደዚያ ልሂድ፡" ብዬ አሰብኩ። አንድ ሰው ወደ እኔ መጣና "አቤት፡ ዛሬ ማታ እጅግ ብዙ አገልግሎት አላቸው፡" አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ "የሰብከት አገልግሎት፡ የመዝሙር አገልግሎት፡ የጸሎት አገልግሎት፡ እና ከዚያም መባ መሰብሰብ ያደርጋሉ፡ ከዚያም እ—እግር መተታጠብ፡ የጌታ እራት፡ እና የጥምቀት ስነ ስርዓት አላቸው፡" አለኝ።

32 "ምስኪን ወንድሜ! አቤት! አቤት፡ ይህ ሁሉ፡ ምናልባት ማለዳ ላይ ከባድ ስብከት ከሰበከ በኋላ፡ ያ ምን ማለት እንደሆነ አውቀዋለሁ፡" ብዬ አሰብኩ። አሁን፡ "ወደዚያ እሄዳለሁ፡ ምናልባት የጌታ እራት እንድሰጥ ይፈልገኝ ይሆናል፡" ብዬ አሰብኩ።

33 እርሱም፡ "ውስጥህ ከሞላልህ ዛሬ ማታ ትሰብከናለህን" ጠየቀኝ? ስለዚህ ምን ማለት እንደሆነ አውቃለሁ። ስለዚህ ወደ ኋላ ተመልሼ መጽሐፍ ቅዱስ ከፍቼ ጥቂት ማስታወሻዎችን ይዣለሁ፡ እና ምናልባት ለአራት ሰዓታት ያህል አጭር መልእክት እንዳሰተላልፍ ጌታ ሊረዳኝ ይችላል፡ በመቀጠል የሚኖረን እ—እ እግር-እንተጣጠባለን፡ ከዚያም የጌታ እራት እናደርጋለን። ከዚያም፡ እንግዲህ፡ ኦህ፡ ምናልባት፡ ከዚያ በፊት እጨርስ ይሆናል። አይዟችሁ፡ ስቀልድባችሁ ነው። ከሃያ፡ ወይም ሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ፡ የጥምቀት ስነ ስርዓት እንፈጽማለን፡ በመቀጠል-... እግራችን፡ ወይም የጌታ እራት ነው? ቀጥሎ የጌታ እራት፡ ከዚያ የጥምቀት ስነ ስርዓት ይደረጋል።

34 አሁን፡ በመጠመቃችሁ ደስ ይለናል። አሁን፣ እግዚአብሔር ቢፈቅድና ደስ ካሰኘው፣ እና ፓስተሩ ፍቃደኛ ከሆነ እና ህዝቡ ፈቃደኛ ከሆነ፣ በሚቀጥለው እሁድ ጠዋት ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ፡ እንደ ጌታ ፈቃድ ለመስበክ፡ እመጣለሁ፡ ምክንያቱም በመጪው እሁድ፡ በሚቀጥለው እሁድ እንደገና ልሄድ ይሆን ይችላል። ስለዚህ፣ እዚህ ሰሆን እዚህ መጥቼ—መሰበክ እወዳለሁ፣ ምክንያቱም እኔና ወንድም ኔቪል፡ ወንድሞች እንደመሆናችን መጠን አንድ ላይ ነን፡ እ—እርስ በርሳችን እንዋደዳለን፣ እ—እ—እጅግ ተቀራርበን መደጋገፍ አለብን...

35 አጉል መንፈሳዊነት ይመስላል፡ በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ እንዳይመስል ተስፋ አደርጋለሁ፡ በአንድ ወቅት ሚስተር ኮሪ እንዲህ አለ፡ እ... ያን ጊዜ እኔ በመብራት ማስታወቂያ ላይ፡ ለኩባኒያው አምፖል እየሸጥኩ ነበር። ለአራት ወይም ለአምስት ዓመታት የሚቆይ እጅግ በጣም ብዙ አምፖሎችን ገዛ፡ እኔም በበኩሌ ከእርሱ ፎርድ ገዛሁ። እሱም "ቢሊ፡ እርስ በርሳችን እየተደጋገፍን

እንደሆነ አምናለሁ፡” አለኝ። እንግዲህ፡ ያም ቢሆን፡ በችግር ጊዜ መርዳዳት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ያም—ቢሆን እውነት ነው። አንዳችን ሌላውን መርዳት እና ለመድረስ እንዴት እንደሚቻል እናውቃለን።

36 አሁን፡ ወደ መልካም ጎኑ እንሂድ፡ ካልተሳሳትኩ፡ ሌላ አገልጋይ ወንድማችን፡ ወንድም ቢለርን ከኋላ እንዳየሁት አምናለሁ። እንዲሁም ዛሬ በግቢው ሳልፍ፡ ወንድም ጁኒ ጃክሰን ከወንድም ክሪክ ጋር ቆመው ነበር። መቼም እዚህ አገልግሎት ይኖራቸዋል አይደል? የጥምቀት አገልግሎት፡ ገባኝ። በጣም ጥሩ፡ ተጠማቂዎቹ ካመጡ ውኃውን ማቅረብ እንችላለን። ው—ውኃውን አዘጋጅተናል።

37 ስለዚህ አሁን፡ የጌታ እራት ስለምናደርግ፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለ ጌታ እራት ብንነጋገር ጥሩ ይመስለኛል።

38 አሁን፡ ወደ ቃሉ ከመክፈታችን በፊት፡ ሁላችንም ሌላ ነገር ሁሉ እናስወግድ፡ የህጻናት እና የጨቅላ ሰራዎቻችን አስወግደን፡ በ—በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ፊት እንቅረብ። እንጸልይ። አሁን አንገታችንን ደፍተን፡ ልባችንንም እንዲሁ፡ እዚህ በእግዚአብሔር ፊት ልታሳውቁ የምትፈልጉት… ሚቀርብ ልመና ካላችሁ፡ እና በእግዚአብሔር ፊት እንዲቀርብላችሁ የምትፈልጉ ነገር ካለ፡ እጃችሁን ወደ እግዚአብሔር በማንሳት አሳውቁት። እግዚአብሔር ለሁላችሁ ያለ ምንም ልዩነት ልመናችሁን ይስጣቸው።

39 ሁሉን ቻይ የሆንከው አምላክ ሆይ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፡ እርሱን ከሞት ያስነሣኸው በግርማውም ቀኝ ያስቀመጥከው፡ እርሱም ስለ እኛ ባደረገልን በምናምንባቸው ነገሮች ላይ ይማልድ ዘንድ ዘወትር ህያው ሆኖ እንደሚኖር፡ እንታመናለን። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ኃጢአታችንን ይቅር እንድትልልን፡ እንጸልያለን። አቤቱ፡ ምን ሊሆን እንደሚችል ስለማናውቅ፡ ሁል ጊዜ በደሙ ስር መቆየት እንፈልጋለን። ጌታ ሆይ፡ ሁሉም ነገር በተግባር እንደተጠናቀቀ፡ የጌታ መምጣት እንደቀረበ፡ ይሰማናል። ጉዞ ለመሄድ ዝግጅት ላይ እንገኛለን። እና ስለ ጉዞ ስናስብ፡ ምናልባት ሻንጣዎችን፡ ስ—ስለ ቅያሪ ልብሶች እና ቅያሪ ጫማዎች እናስባለን። ይሄኛው ግን ከዚህ አይነት ጉዞ ምንኛ የተለየ ነው! ሸክምን የማቃለል፡ የማራገፍ እንጂ፡ የመሸከም አይደለምና። ታላቁ አገልጋይህ፡ ጳውሎስ፡ በዕብራውያን መልእክት፡ ምዕራፍ 12 ላይ፡ “በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንድንሮጥ፡ ሸክምን ሁሉ እና ቶሎ የሚከበንን ነገር ሁሉ እናስወግድ” አለ።

40 እና አሁን ለዚህ ዘመናዊ ዓለም መልካም ነገር መተንበይ አንችልም። በመንፈስ መተንበይ የምንችለው ብቸኛው ነገር አደጋ፣ ችግር፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ታላቅ ማዕበል፣ ፀሐይና ጨረቃ መጨለም፣ ክርስቶስ ከውጭ ሆኖ፡ መግባት ፈልጎ የሚያንኳኳባት፣ በሎዶቅያ ዘመን ያለች ቤተ ክርስቲያንን ነው። አምላክ ሆይ! ልክ እንደ ሚክያስ፡ ትንቢቱ በተቃራኒ ሲሆን ሳለ አክዓብን እንዴት ሊባርከው ይችላል? ያ ታላቅና ኃያል ነቢይ፡ ኤልያስ፡ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፡ የዚህን ንጹሕ ሰው የናቡቴን ሕይወት ስለ ቀጠፈ፡ ያን ጊዜም፡ “ውሾች ደምህን ይልሳሉ፡” ተባለ። ታዲያ ሚክያስ መልካም ነገሮችን እንዴት ሊተነብይለት ይችላል?

41 የዛሬዎቹ በመንፈስ የተሞሉ-ልጆች ጌታን ለጣሉት ለኃጢአተኛና፡ ግድ ለሌላቸው ሰዎች መልካም ነገር ሊተነብዩ የሚችሉት እንዴት ነው? አቤቱ አምላክ ሆይ፡ በፊታችን የምናየው የፍርድን መራራነት ብቻ ነው። እኛም በቅንነት ለማይሄዱት እናለቅሳለን፡ “በጥም ምድር ውስጥ አለት ነውና፡ ወደ እግዚአብሔር ሽሹ! እርሱ በዐውሎ ነፋስ መካከል መጠጊያ ነው። የእግዚአብሔርም ስም የጸና ግንብ ነው፡ ጻድቃንም ወደ እርሱ ሮጠው ይድናሉ።” ስለ እነዚህ ስለ ተገነቡት ታላላቅ የመማጸኛ ከተማዎች፡ ስናስባቸው፡ አሳዳጅ ሲከተለው... ሰውዬው አንዴ ግንቡ——ውስጥ ከገባ በኋላ፡ ደህና ይሆን ነበር፡ ማንም አይጎዳውም ነበር። አምላክ ሆይ፡ እርሱ መጠጊያችንና ኃይላችን፡ በችግር ጊዜ ፈጣን ረድኤታችን ነውና፡ አቤቱ ወደ ጌታ እንቸኩል ዘንድ እርዳን። ስለዚህ፡ በንስር አይን ስናየው፡ እንደ ቀድሞ፡ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፡ ደመናው ሲሰበሰብ፡ የፍርድ ነጐድጓድና መብረቅ በምድር ላይ ሲወርድ፡ አውሎ ነፋሱ ቅርብ እንደሆነ እናውቃለን።

42 ዛሬ ማታ፣ ጌታ ሆይ፣ እዚህ እጃቸውን ላነሱት እንጸልያለን። አባት ሆይ፡ ምን እንደሚፈልጉ እኔ አላውቅም፡ አንተ ታውቃለህ። የእጆቻቸውን መነሣት ትርጉም የሆነው፡ ለውድ ነፍሳቸው የሚያስፈልግ ሁሉ እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ባርከን። የታመሙትን ፈውስ። የደከሙትን አጽና። ለተጨቆኑት ደስታን ስጥ። ለደካከሙት ሰላምን ስጥ፡ ለተራቡት መብልን፡ ለተጠሙት ውኃን፡ ላዘኑ ደስታን፡ ለቤተ ክርስቲያን ኃይልን ስጥ። ጌታ ሆይ፡ የተቆረሰውን አካሉን ተምሣሌት የሆነውን የጌታ እራት ለመቀበል በምንዘጋጅበት ወቅት፡ ኢየሱስን ወደ መካከላችን አምጣው። ጌታ፡ በልዩ ሁኔታ እንዲጎበኘን፡ እንጸልያለን።

43 ይህችን ትንሽ ጉባኤ፣ የተወደደው ፓስተር፣ ወንድማችን ኔቪልን እና ቤተሰቡን፣ ዲያቆናትን፣ ባለአደራዎችን፣ እና የተገኙትን ሁሉ ባርክ። ሌሎችን ባርክ፡ ጌታ ሆይ፡ የጌታን መምጣት በደስታ የሚጠባበቁትን፡ በዓለም ሁሉ ያሉትን፡ መብራቶች አዘጋጅተው፡ ጭስ ማውጫዎቻቸውን የወለወሉ ሁሉ፡ የወንጌል ብርሀን በጨለማ ቦታዎች የሚያበሩ ሁሉ ባርካቸው።

44 አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ እኔም እነዚህን ጥቂት ቃላት እንድናገር፡ እርዳኝ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና፡ ስናነበው ባርክልን፡ አውዱንም ስጠን። ኣሜን።

45 አሁን መፅሃፉን ገልጠን፡ ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ እንውሰድ፡ እና እያንዳንዳችን ቤት ስንደርስ ሙሉውን ምዕራፍ ብናነብ ጥሩ ይሆናል። ከ47ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ ማንበብ እፈልጋለሁ፡ በአጠቃላይ እስከ ቁጥር 59 ድረስ፡ ማንበብ እወዳለሁ፣ ይህም **የጌታ እራት** በሚል ርዕስ፥ መሠረት ለመገንባት ይሆነኛል።

አሁን በዚህ በዓል ላይ የተናገረው፡ ኢየሱስ ነው። እነዚያ በዓላቶች፡ እጅግ የተከበሩ ነበሩ። ከዓለት ውስጥ ውሃ መጠጣታቸውን፡ በበረሃ የነበረውን አለት ምሳሌውን ለማድረግ ነው። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የወረደውን መና ለማስብ፡ መብልን፡ ይበሉ ነበር። ልክ ዛሬ ምሽት እንደምናደርገው፡ የፋሲካ በዓል ነበር።

> **እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።**
>
> **ያ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።**

**አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፡ ሞቱም።**

**ሰው ከእርሱ በልቶ፡ እንዳይሞት፡ ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው።**

**ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፥ ማንም ከዚህ እንጀራ ቢበላ፡ ለዘላለም ይኖራል፥ ስለ ዓለም ሕይወት፡ እኔ የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።**

**አይሁድም ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ሊሰጠን እንዴት ይችላል? ብለው፡ እርስ በርሳቸው ተከራከሩ።**

**ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፡ ደሙንም ካልጠጣችሁ፡ በራሳችሁ ህይወት የላችሁም።**

**ሥጋዬን የሚበላ፡ ደሜንም የሚጠጣ፡ የዘላለም ሕይወት** አለው፥ **በመጨረሻውም ቀን እስነሣዋለሁ።**

**ሥጋዬ በእውነት መብል፡ ደሜም መጠጥ ነውና።**

**ሥጋዬን የሚበላ፡ ደሜንም የሚጠጣ፡ በእኔ ይኖራል፡ እኔም በእርሱ እኖራለሁ።**

**ሕያው አብ እንደ ላከኝ፡ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ፡ በእኔ ሕያው ይሆናል።**

**ከሰማይ የወረደው እንጀራ ይህ ነው፥ አባቶቻችሁ መና በልተው፡ እንደ ሞቱ አይደለም፥** ይህን **የሚበላ ግን... ይህ እንጀራ ለዘላለም ይኖራል።**

**በቅፍርናሆም ሲያስተምር፡ ይህን በምኩራብ ተናገረ።**

46 ጌታ ቃሉን ይባርክ። ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፡ በ **ጌታ እራት** ላይ፡ መናገር፡ እፈልጋለሁ። Communion የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? Commune ማለት "መግባባት" ማለት ነው። ምን ማድረግ፡ መ... communion ማለት "ሕብረት ማድረግ፡ አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባት" ማለት ነው። ከአንድ ሰው ጋር በስልክ ብታወሩ፡ ውይይት ታደርጋላችሁ፡ እርስ በርሳችሁ እየተግባቡ ነው ይባላል። ለምሣሌ አንድ ግለሰብ እና ፓስተር፡ በህንጻው በስተጀርባ ለብቻቸው ነጠል ብለው ቢሄዱ፡ ወይም ማንኛቸውም ሁለት ሰዎች ቢሄዱ፡ አንዱ ከሌላው ጋር እየተግባቡ ነው እንላለን።

47 እንግዲህ፡ በራዲዮ፡ ወይም በቴሌቪዥን፡ መግባባት አንችልም። በቴሌፎን ግን... ትችላላችሁ፡ ምክንያቱም ከአንዱ ወገን ብቻ ሳይሆን፡ አንዳችሁ ከአንዳችሁ ጋር እየተግባባችሁ ስለሆነ ነው። ያ ነው... ለምሣሌ አሁን እናንተ ስለማትመልሱልኝ፡ ከእናንተ ጋር እየተግባባን አይደለንም። ስለዚህ፡ አገልጋይ መልእክቱን ለማስተላለፍ ሲመጣ፡ እርሱን ለመስማት መምጣት አይደለም። ያንን አንድ ላይ ለመግባባት፡ መምጣት፡ ሊሆን አይችልም። የጌታ እራት ማለት ያንን አይደለም... ከአገልጋይ ጋር ንግግር ለማድረግ ከመጣችሁ፡ እርሱን ወይም ማንም ሰው፡ ወደ አንድ ጥግ ትጠሩታላችሁ፡ ከዚያም ከእሱ ጋር ወይም ከእሷ ጋር ትነጋገራላችሁ።

48 እኛ አሁን የጌታ እራት፡ የምንለው ነገር ግን፡ እያንዳንዳችን በየግላችን ከክርስቶስ ጋር ያለን መግባባት ነው። ይህ መግባባት ይባላል። ስለዚህ፡ ሁላችንም ስንግባባ ነው እንጂ፡ **አንዱ** ወገን ብቻውን ተናጋሪ በሚሆንበት ሁኔታ መግባባት አይባልም። ነገር ግን የሚለንን እናያለን እንጠብቃለንም።

49 እንግዲህ፡ ብዙ ጊዜ፡ ታላላቅ ስህተቶች የምንሰራበት ስፍራ፡ እዚህ ጋር ነው፡ ይህም፡ እኛ ብቻ ሁሉንም እንናገራለን እርሱ እንዲመልስን ግን እድል አንሰጠውም። አንዳንድ ጊዜ፡ እንዲህ እንላለን፡ "ጌታ ሆይ፡ **ይህን-እና-ያንን** እንዲሁም **ይህን-እና-ያንን** እንድታደርግልኝ እፈልጋለው፡ አሜን፡" ብለን ተነስተን እንሄዳለን። እንግዲህ፡ ያ መግባባት አይደለም። ውለታን መጠየቅ ነው እንጂ። ነገር ግን እሱ እስኪመልስ ድረስ ብዙ ስትቆዩ፡ ያኔ ወደ ኅብረት፡ ከጌታ ጋር ወደ እራት ኅብረት የምትመጡበት ጊዜ ነው። አሁን፡ ትልቁ የመግባባት መንገድ፡ በመስማማት ነው፡ በአንድ ነገር ላይ መስማማት ያስፈልጋችኋል። አንዳንድ ጊዜ ወደ እነዚህ ነገሮች ስንገባ፡ እንግዳ ነገሮች ናቸው...

50 ከዚህ በተጨማሪ መብላት ከዚህ ጋር ይያያዛል። ለምሳሌ፡ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን እንውሰድ፡ ውል ለመዝጋት ሲፈልጉ፡ ሰውየውን ወደ ምግብ ይጋብዛሉ። ከዛ በኋላ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጠው ይበላሉ፡ ከዚያም አብረው ያወራሉ። በመሰረቱ ጥሩ የሽያጭ ሰራተኛ፡ ባዶ ሆድ ያለውን ሰው አያነጋግርም። ጥሩ ስሜት እስኪሰማው፡ እና ቁርስ እስኪበላ ድረስ መጠበቅ ጥሩ ነው። ገና ከአልጋው አውርደህ ልትሸጥለት ስለምትፈልገው ነገር ገለጻ ለማድረግ አትሂድ፡ ነገር ግን ቁርሱን እስኪበላ ድረስ ጠብቀው እ—እና ሁሉ ነገር ዝግጁ አድርገው።

51 በቀደም፡ የኢየሱስን እግር ስለታጠበችው ሴት ስሰብክ፣ ካናዳ ውስጥ ነው ስለዚህ ነገር እያወራሁ ነበር፡ እንግዲህ አንድ እንግዳ ሰው ሊጠይቅ ሲመጣ፡ ይህ ሰው ለመጠየቅ ወይም ለመግባባት መሄድ አለብኝ ብሎ ከማመኑ በፊት፡ ማለፍ ያለበት፡ የተወሰኑ ሂደቶች ነበሩ። መጠየቅም መግባባት ነው። ስለዚህ፡ ወደዚያ ሲመጡ... መጋበዝ፡ ከሁሉ በፊት መጋበዝ አለባቸው። ከዚያ በኋላ ወደ በሩ ትጠጋለህ አገልጋይ የሆነው ሰው እግርህን ያጥባል፡ በጉዞው ምክንያት፡ በመንገድ ላይ የ—የእንስሳት እና የመንገድ የሌሎች ነገሮች ሁሉ ሽታ ታነሣለህና። ሰዎቹ ሁሉ... ከእንስሳት ጋር በተመሳሳይ መንገድ ይጓዙ ነበር፡ እ—እና ሽታው እና አቧራው ሁሉ አለ፡ በተጨማሪም የፍልስጤም ልብስ እየሳበ ወደ እግር ላይ ያከማቻቸዋል፡ እንዲሁም ፊት፡ እ—እና እጆች አይሸፈኑም። እ—እና በደጅ አፉ ላይ ያራግፏቸዋል፡ አገልጋዩ ያራግፋቸዋል፡ እግራቸውንም ያጥባል። ከዚያም ሌላ ሰው ፎጣና የአልባስጥሮስ—ብልቃጥ ይዞ ይቆማል፡ ይህንም አላባስጥሮስ በእጃቸው ላይ በማድረግ፡ **እንዲህም** እያሻሹ፡ በ—በፊታቸው ዙርያ ላይ ያሹታል፡ ከዚያ በኋላ ሁለመናቸውን በፎጣ ይጠራርጋሉ። ያም ቆሻሻውን እና ሽታውን ሁሉ ያስወግደዋል። ያም ልክ እንደ ሜንታ፡ እረፍት እንዲሰማቸው የሚያደርግ ነገር አለው፡ ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋቸዋል።

52 ከዚያ ወደ ውስጥ ሲገቡ፡ በእነዚያ ጥሩ ምንጣፎች ላይ፡ ያረጁ የቆሸሹ ጫማዎችን ለብሰው ሳይሆን፡ በሚዘጋጅላቸው፡ የቤት ነጠላ ጫማ መሣይ፡ ወደ ውስጥ ይገባሉ። እንግዳው—በዚህ ሁኔታ ይገባል—ጋባዡም—እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ይስማቸዋል። ስለዚህ፡ ተመልከቱ፡ ከመጥፎ ጠረናችሁ ጋር

ጋባዡ እንዲሰማችሁ መቼም አትፈልጉም። ቆሽሻችሁ ምንጣፍ ላይ መራመድ መቼም አትፈልጉም። ከዚያ በኋላ ጋባዡ ይሰማችኋል፡ ያን ጊዜ የቤቱ አካል ትሆናላችሁ።

53 ስለዚህ፡ አሁን፡ እግዚአብሔርም እንዲህ ያሉ ልምምዶች አለው። ከእግዚአብሔር ጋር ወደ እራት ለመግባት፡ በእውነት ዝግጁ ከመሆናችን በፊት፡ በመጀመሪያ በቃሉ ውሃ መታጠብ አለብን። ከኃጢአታችን በሚለየን በመለየት ውሃ፡ መለየት። አሁን፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ከሰራህ ሁሉ ንስሓ መግባት አለብህ፡ ካልሆነ... በመሰረቱ፡ ከእግዚአብሔርም ጋር መነጋገር አትችልም፡ ምክንያቱም "ጌታ ሆይ፡ አለማመኔን ይቅር በለኝ፡" ብለህ ንስሓ እስካልገባህ ድረስ በትክክል ማመን አትችልም። እያችሁ? "አለማመኔን ይቅር በለኝ።" በመጀመሪያ ደረጃ፡ ንሰሐ ግባ። እናም፡ ንሰሐ ስትገቡ፡ ከዚያ በኋላ... የኋላ ኃጢአታችሁ ይተውላችኋል፡ ከዚያ በኋላ ለጥምቀት እጩ ትሆናላችሁ። እንግዲህ፡ ከጥምቀት በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስን ቃል ገብቷል።

54 አሁን፡ እንግዲህ፡ ነገሩ፡ በዚህ አይነት ግብዣ ላይ፡ ከዚህ ጎን ለጎን፡ በተጨማሪ፡ እግራችንን የምንታጠብበት የእግር-መተጣጠብ እ—እንደነበረ አስተውለናል፡ ይህም እንደ የመንፈስ ቅዱስ ንጽሕና ምልክት ነው።

55 በተጨማሪም፡ ደግሞ፡ በሁለቱም ወገን የጋራ ስሜት መኖር አለበት። ከ—ከጋባዣችሁ ጋር ጠርዝ ላይ ከደረሳችሁ፡ መ—መመገብ አትችሉም። አይ፡ አ—አትችሉም፡ ምክንያቱም ከእሱ ጋር አልተሰማማችሁም። ከተሰማማችሁ ግን፡ መመገብ ትችላላችሁ። ስለዚህ ወደ ጌታ ማዕድ ስንመጣ እንደዚያ ነው፣ ከቃሉ ጋር መስማማት አለብን። እያችሁ? ዳግመኛ መወለድ አለብን፡ በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ እርሱ ለጻፈው ቃል ሁሉ "አሜን" ማለት አለብን፡ ከዚያ በኋላ ከእርሱ ጋር መመገብ እንችላለን።

56 ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ አለን፡ ልባችን ባይፈርድብን፡ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አለን። ልባችን ስለማይወቅሰን፡ ልመናችንን እና ፍላጎታችን እንደምናገኝ እናውቃለን። እንግዲህ፡ ዳግመኛ መወለድ እንዳለብን እግዚአብሔር ከነገረን፡ እኛም አዲስ ልደት ካልተቀበልን፡ ምክንያቱም የእሱን መስፈርቶች እንዳላሟላን ስለምናውቅ፡ ከሱ ዘንድ ለመለመን፡ እያችሁ፡ ትንሽ እንግዳ ስሜት ይሰማናል። የኃጢአተኛ ጸሎት ብቻ ይሆንብናል። ከእሱ ጋር በሕብረት ሳለን እርሱን ስናነጋግረው ግን፡ ያ ወደ ጌታ እራት ያደርሰናል።

57 ስለዚህ፡ የጌታ እራት ማለት ይህ ነው፡ ይህን ለማብራራት ጥቂት ጊዜ መውሰድ ነበረብኝ። አሁን፡ ይህን፡ **የጌታ እራት** ስንል፡ ወይኑ እና ህብስቱ ይመስለናል። አሁን፡ በዚህ ርዕስ መናገር እስከማይቻል ድረስ እጅግ የተዛባ ነገር ሆኖ ቆይቷል። አቤት፡ ባለፉት ዓመታት ምን ያህል የተዛባ ሆኖ ኖረ! ያኛው ትእዛዝ መጠበቅ ብቻ ነው እንጂ፡ የጌታ እራት ያ አይደለም። እያችሁ? እንግዲህ፡ እኛ የጌታ እራት ያልንበት ምክንያቱ፡ ከካቶሊክ ድርጅት ስለመጣ ብቻ ነው ይህም በእነሱ ዘንድ፡ "ቅዱስ ቁርባን፡ ማለትም በጥሬው የጌታ ኢየሱስ አካል" ይባላል። ይሁን እንጂ ይህ የአካሉ ማስታወሻ ነው እንጂ። የጌታ ኢየሱስ አካል አይደልም!

58 ምንም ያህል ካህናት ወይም ሰባኪዎች፡ ወይም ማንም ቢባርከውም እንኳ፡ ህብስት እና የወይን ጠጅ ከመሆኑ አያልፍም። እንደ እኛ ካህን የለም... ይሉናል፡

“ካህኑ የጌታን እራት ሲያስቀብል እግዚአብሔር ይሰማዋል፡” ይላሉ፡ እነሱ የጌታ እራት የሚሉት ግን፡ “ቁርባን፡ ያው ራሱ የጌታ ኢየሱስ አካል ነው። አማኙም ይቀበለዋል፡ ያም የጌታ እራት ይባላል።” ስሕተት ነው!

59 Commune ማለት “መግባባት፡ መነጋገር፡ ተናግረኸው የሚመልስልህ ነገር ነው።” መግባባት ማለት ያ ነው። መቼም ህብስት አይመልስልህም። ስለዚህ፡ እውነተኛው የጌታ እራት፡ መንፈስ ቅዱስ መልሶ ሲያነጋግርህ ነው። ስትጠይቀው፡ እሱ መልሶ ይናገራል፣ ትክክለኛው የጌታ እራት ያ ነው። **ይሄኛው** መታሰቢያ ነው፡ ከዚህ መቀበል… ከስቅለቱ እና ከትንሳኤው መውሰድ፡ የጌታ እራት አይደለም። ብለን እንጠራዋለን እንጂ፡ አይደለም። በቀደም ስለ ስርዓት ስንማር እንዳየነው ከዚህ ህብስት መውሰድ፡ ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን የመጣ ነው፡ **የጣኦት አምልኮ እና ክርስትና** በሚል ርዕስ ላይ አይተነዋል።

60 “ትንሿ ክብ ህብስት በጥሬ የክርስቶስ አካል ናት ይሏታል።” ይህን የምታምነው፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት። በቤተ ክርስቲያን በኩል ሲያልፉ፡ የመስቀል ምልክት ሲያደርጉ፡ ቆባቸውን፡ እና ሌላ ነገር ሲያነሱ፡ አስተውላችኋል? ቤተ ክርስቲያኒቱን አይደለም፡ ህብስቱ ነው፡ “ካህኑ ከህብስት ወደ ጥሬ የክርስቶስ አካል ለለወጠው ለዚያ አካል ነው፡” ያም አይጦች እና መጎጦች ሊዘነጣጥሉት የሚችሉት ነገር ነው። እንዴ፡ ምነው፡ እንደ ተራ ሰው ብታስቡት እንኳ ቁራሽ እንጀራ የጌታ የኢየሱስ ሥጋ ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም! ሊሆን አይችልም።

61 **የጌታ እራት** ማለት “ከምትናገረው አካል ጋር፡ መናገር፡ እና መግባባት ነው።” Commune የሚለው ቃል “ሌላ አካልን ማነጋገር፡” ወይም፡ “መልስ ለመስጠት ከሚግባባችሁ ጋር ህብረት ማድረግ ማለት ነው።” እግዚአብሔርም ይመልስላችኋል፡ የጌታ እራት። እኛ ግን አሁንም **የጌታ እራት** የምንለው፡ ወይኑን እና ህብስቱን ነው።

62 አሁን፡ ኢየሱስ እዚህ ላይ ሳነበው፡ እንዲህ አለ፦ “ሰውነቴ መብልና መጠጥ፡ ደሜም፡ ሰውነቴና ደሜ መብልና መጠጥ ናቸው።”

63 አሁን፡ ኢየሱስ በሆነው ነገር ላይ፡ እሱን ማሰብ እና ከእሱ ጋር ህብረት ማድረግ ያስፈልገናል። አካሉ ምንድን ነው? የክርስቶስ አካል ምንድን ነው? በመንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር አንድ አካል የሆኑት የአማኞች አካል ነው። ጣዖት አይደለም፡ ቁራሽ እንጀራም አይደለም፡ ነገር ግን በአማኙ ልብ ውስጥ ያለ መንፈስ ነው፡ አንድ ላይ ይተባበራሉ፡ ይህም ማለት ሰው እና እግዚአብሔር እርስ በርሳቸው ሊነጋገሩ ይችላሉ፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ናቸው። ደሙ መፍሰሱ፡ ለሟች ሰው የኃጢአት ስርየትን አመጣ፡ እናም ወንዱም ሴቷም፣ ወጣቱ እና ልጃገረዷ፡ ከክርስቶስ ጋር የወንድማማችነት ግንኙነት ያላቸው ሁሉ፡ ከእርሱ ጋር፡ ከአካሉ ጋር ህብረት አላቸው።

64 ባልና ሚስት ወይም ወንድ እና የሴት ጓደኛ፡ ለመነጋገር አብረው እንደሚቀመጡ፡ እንዲሁ ክርስቶስ እና ቤተክርስቲያኑ ህብረት ያደርጋሉ። ስለዚህም ከእርሱ መስማት የቻልነው፡ ከመሆኑ በፊት የወደፊቱን ማወቅ የቻልነው፡ እንዲሁም የወደፊቱን ያለ አንዳች ስህተት መናገር የቻልነው፡ ዘለአለማዊነትን በእጁ ከያዘው አምላክ ጋር ህብረት ስላለን ነው። በክርስቶስ አካል፣ መንፈሳዊ በሆነው፣ ምስጢራዊው በክርስቶስ አካል፡ እርስ በርሳችን

ህብረት አለን። ከየትኛውም ጣዖት፡ ወይም ህብስት ወይም ወ—ወይን ጋር አንድነት የለንም፡ ነገር ግን በ—በመንፈሳዊ መልክ ነው።

65 አሁን፡ ኢየሱስም እንዲሁ ተናግሯል። በጉድጓዱ አጠገብ ከሴት ጋር ሲነጋገር፡ የዮሐንስ ምዕራፍ 4ን፡ ውሰዱ፡ እንዲህ እያለች አነጋገረችው፡ "አባቶቻችን ከዚህ ምንጭ ጠጡ፡ ይህን ጉድጓድም ቈፈሩት፣ ያዕቆብም፡ ከዚህም ውኃ ለ—ለልጆቹ እና ለከብቶቹ ከዚህ ውኃ አጠጣቸው፡ እነሆ አንተ፡ '**በሆነች** ከተማ ላይ እንሰግድ' ትላለህ፡ ሌሎች ደግሞ፡ 'በዚህ ተራራ' ይላሉ።"

66 ኢየሱስም ምንም—እንኳ እንዲህ ቢናገሩ፡ "ይኸውልሽ! ይህ ምን ማለት እንደሆነ፡ አምልኮ ማለት ምን እንደሆነ፡ እኛ አይሁዶች እናውቃለን። አንቺ ሴት ግን፡ ይህን ሰሚ። እውነተኛ አምላኪዎች ግን፡ እግዚአብሔርን በእውነት እና በመንፈስና የሚሰግዱበት ጊዜ መጥቶአል፡ ጊዜው አሁን ነው። 'ቃልህ እውነት ነው።' አብ የሚፈልጋቸው፡ በመንፈስና በቃሉ በእውነት የሚያመልኩትን ነው። 'ቃልህ እውነት ነው።'" አሁን፡ ለዚች ሴት የነገራት ይህንኑ ነው።

67 ተመልከቱ፡ ክርስቶስ... እግዚአብሔር መንፈስ ነው። **ክርስቶስ** ማለት "የተቀባ፣ በእግዚአብሔር የተቀባ ሰው" ማለት ሲሆን፡ ይህም እርሱን ክርስቶስ አድርጎታል። አሁን ክርስቶስ፣ "እኔ መብልና መጠጥ ነኝ፡" አለ። እንጂ ህብስት ነኝ አላለም፡ እዚህ እኛ የምንቀበለው አይነት ህብስት አይደለም። ያ ክርስቶስ አይደለም። በመሠዊያው ላይ የምንጠጣው ወይን፡ ክርስቶስ አይደለም። በምሳሌያዊ መንገድ፡ እርሱን ይወክላል። ክርስቶስ ግን መንፈስ ቅዱስ ነው፡ በቤተክርስቲያን ላይ ያለው ቅባት፡ መብልና መጠጥ እርሱ ነው።

68 በዓለም ላይ ያለ አንድ ትልቅ ጩኸት አለ፡ አንዳችሁም ሰምታችሁት እንደማታውቁት ተሰፋ አደርጋለሁ፡ ከሰማችሁ፡ ግን፡ ከረሃብ ጩኸት ጋር ሊወዳደር የሚችል ጩኸት የለም። እናት ልጇን ይዛ፡ ከድካም ብዛት መራመድ አቅቷት፡ ህጻን ልጇ ሞት አፋፍ ሆኖ ሰትመለከቷት፡ ከረሃብ የተነሣ ሆዱ አብጦ፡ ከእናንቲቱ ልብ የሚሰማ ሲቃ፡ ህጻኑም አጥንት እና ቆዳ እስኪቀር ድረስ ጉንጮቹ አልቀው፡ ድዱ ብቻ እስኪታይ ቀርቶ፡ ትንሽሽ ዓይኖቹ አግጥጠው፡ ድምጽ ማሰማት አይችልም፡ በጭራሽ። እንደ ረሃብ እና እንደ ጥም የሚያስለቅስ ነገር የለም።

69 በዚያ በምድረ በዳዎች፡ ሰንት ሰዎች በውኃ ጥም ህይወታቸውን አጥተዋል! ሌሊቱን ሙሉ ላሰቀምጣችሁ የምችልበት፡ ብዙ የበረሃ ታሪኮች አሉኝ፡ እውነተኛ ታሪኮች። ሰንቶቻችሁ ገጥሟችሁ ያውቃል... ሰትጠሙ፡ ዲያብሎስ ከሩቅ የ—የሚብለጨለጭ ነገር ያሳያችኋል። እዚሁ ራሱ ማየት ትችላላችሁ፡ ያንን ለማየት ወደ ምዕራብ መሄድ አያስፈልጋችሁም። ወደ መንገድ ውጡና፡ በመንገዱ ላይ ውሃ ያለ ይመስላችኋል። ሃይዌ ላይ መኪናን የምትነዱ ሁላችሁ፡ ይሄንን አይታችኋል። የውሸት ብልጭልጭ ነው። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ከሦስትና ከአራት ዓመታት በፊት፡ በአገሪቱ ላይ ስለሚበርሩ፡ አንዳንድ ዳክዬዎች፡ የሚብለጨለጨውን እያዩ፡ ወደ ውኃው ውስጥ እየዘፈቁ መሰሏቸው በመንገድ ላይ ተጋጭተው እንደነበር አንብቤያለሁ። በብልጭልጩ ምክንያት፡ በውኃ ላይ እናርፋለን ብለው በማሰብ፡ ደረቅ መንገዱን እየመቱ፡ ተፈጠፈጡ።

70 ዲያቢሎስ በሰዎች ላይ ስንት ጊዜ ያንኑ ነገር አደረገ፡ የውሸት ብልጭልጭ ይሰጣቸዋል፡ በዚያም፡ ተራ አስመሣይ—አማኝነት ነው እንጂ፡ አንዳች ነገር የለውም። ዛሬ ብዙ ሰዎች አስመሣይ—አማኝነትን ተቀብለዋል። የሆነ ነገር ለማድረግ መሞከር ወይም የሌለውን ነገር እንዳለ ለማስመሰል መሞከር! ልክ ሚሰዮናዊቷ እንደተናገረችው ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ እስክሆን ድረስ እጠብቃችኋለሁ አለች። እንደዚያ ማድረግ ይሻለናል። ተመልሳችሁ ሙከራ ማድረግ አያስፈልግም። አንድ ዕድል ስታገኙ፡ ብሉፕሪንቱን ያዙ፡ ስለዚህ በቀጥታ ወደ ምልክቱ መዘርጋት ይሻላል።

71 የራብ ጩኸት፡ ይኸውላችሁ፡ የጭንቀት ጩኸት ነውና ታላቅ ጩኸት ነው። ሰውዬው እየሞተ ነው። አቤት፡ እንደው፡ እኛ ወደዚያ አይነት ሁኔታ፡ ይህች አገር እንደዚሁ እግዚአብሄርን የምትራብበት ሁኔታ ውስጥ በገባች ኖሮ! በአካል ከሚራቡ እንደ ህንድ ካሉ ሀገራት የባሰ ረሃብ ድርቅ ነው፡ ይህች አገር በመንፈሳዊ ድርቅ ውስጥ ናት። ይሁን እንጂ እጅግ ከተራባችሁ በኋላ፡ መራባችሁን ወደማታስተውሉበት ሁኔታ ያደርሳችኋል።

72 ልክ እንደ ኃይለኛ ቅዝቃዜ ነው። እጅግ፡ ከቀዘቀዛችሁ በኋላ፡ በጣም በጣም ይበርዳችኋል፡ ከጊዜ በኋላ ይሞቃችኋል። በዚያን ጊዜ፡ እየሞታችሁ ነው! የዛሬ ምሽት ችግርም ይሄው ነው። አብያተ ክርስቲያናቱም በረዶ እስኪሆኑ ድረስ በጣም ቀዝቅዘዋል፡ አባል በመሆን፡ የሚሞቃቸው ይመስላቸዋል፡ በመንፈስ ግን እየሞቱ ይገኛሉ። ይሞታሉ! አያውቁትም። ውሎ አድሮ፡ ሰውዬው ይተኛል፡ መጨረሻውም ያ ነው። ደሙ በደም ሥሮች ውስጥ ስለቀዘቀዘ፡ ከእንግዲህ አይነቃም።

73 ይኸው፡ መጠማት። ኢየሱስ "ደሜ በእውነት መጠጥ ነው፡" ብሏል። ሕይወትን ከተራባችሁ፡ ሕይወት ከራባችሁ፡ ጥማችሁን የሚያረካ ብቸኛው ውኃ ኢየሱስ ብቻ ነው። "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ።" በራዕይ ላይ ደግሞ፡ "የተጠማ ወደ ሕይወት ውኃ ምንጭ ይምጣ በነፃነትም ይጠጣ፡" ይላል። ሕይወትን የተጠማ!

74 የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች፡ በተወሰነ በወሩ መጀመሪያ ወይም የመጀመሪያ ክፍል፡ ከሁለተኛው ወይም ከአምስተኛው፡ ወይም ከዚህ ወር ጀምሮ፡ የሕንድ የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ዓለም ተቆራርጣ ትደቃለች ብለው ሲተነብዩ እንመለከታለን። የአሜሪካ ጋዜጦችም ያሾፉበታል። እኔም ብሆን አለም ወደ ቁርጥራጭ ትደቃለች ብዬ አላምንም፡ ቢሆንም በዚ መቀለድ ስህተት ነው እላለሁ። ምክንያቱም፡ ከነዚህ ቀናት በአንዱ እንደዚህ ያለ፡ የሆነ ነገር ሊፈጠር ነው፡ አምስቱ ፕላኔቶች፣ ማርስ፣ ጁፒተር እና ቬኑስ፣ እ—እና የመሳሰሉት፡ ወደ አንድ ነገር—ውስጥ ይገባሉ... ከዚህ በፊት አድርገውት አያውቁም። መቼም፡ ከሃያ-አምስት ሺህ ዓመታት በፊት ይህ ሆኖ ነበር ይላሉ፡ ይሁን እንጂ ያኔ ማን ያውቀዋል?

75 ይህ መንፈሳዊ አተገባበር እንዳለው ተንብዬአለሁ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ታላቁ የቃሉ መገለጥ ይከፈታል የሚለው፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ መግቢያ ነው ብዬ አምናለሁ። አስታውሱ፡ ኢየሱስ ሲወለድ ሦስት ኮከቦች እርስ በርሳቸው ወደ ምህዋራቸው እንደገቡ ይናገራሉ። በዚህ ጊዜ አምስት ሲሆኑ፡ አምስት ደግሞ፡ የጸጋው ቁጥር ጸጋ ነው። ሦስት የፍጹምነት ቁጥር ነው። አምስት

የጸጋ ቁጥር ነው፡ J-e-s-u-s፣ g-r-a-c-e፣ f-a-i-t-h፣ እና የመሳሰሉት። የጸጋ ቁጥር! እግዚአብሔር ኃይሉን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከላከ፡ ከጸጋው የተነሣ ነው እንጂ፡ በሰዎች መታዘዝ ምክንያት አይሆንም። ኢሳይያስ፡ በምዕራፍ 40 ላይ፡ "ጦርነትዋ እንዲያበቃ፡ ወደ ኢየሩሳሌም ጩኹ" ብሏል፡ በጣዖት አምልኮ ጥፋተኛ ብትሆንም፡ ያደረሳት ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። እግዚአብሔር ምንም ነገር ከላከልን፡ ከጸጋው የተነሣ ነው እንጂ በእኛ ስራ አይደለም። ስለዚህ፡ አንድ ነገር ሊሆን ይችላል። ለውጥ ይኖራል ብዬ እገምታለሁ። ምን እንደሚከሰት አላውቅም፡ ሊሆን እንደሚችል ግን አምናለሁ። አሁን በዋዜማው... ላይ ነን።

76 እንግዲህ ማንም የተራበ ቢኖር፡ ወደ ክርስቶስ ይምጣ። የተጠማ ቢኖር፡ ወደ ክርስቶስ ይምጣ። ጥማትን የሚያረካ እርሱ ነው። ጥማችንንና ረሃባችንን ሙሉ በሙሉ የሚያረካ እርሱ ነው።

77 ከተወሰነ ጊዜ በፊት አንድ ታሪክ ተነግሮኝ ነበር። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስቀድሜ ተናግሬ ይሆናል። ከሆነም፡ አንድ ነጥብ ላይ ለማጉላት በመድገሜ ይቅር በሉኝ። የሕንዶች አስጎብኚ፡ ወይም፡ ለህንዶች የበላይ ተጠሪ የሆነ አንድ ሰው ነበር። እርሱም በናቫሆ ምድር እየተጓዘ ነበር፡ እና፡ ጠፋ። ሰሙ ኮይ ይባላል። ዱካ ተከትሎ ይሄድ ነበር፡ የዱር እንሰሳት ዱካ እየተከተለ ነበር፡ እና በልቡ፦ "አሁን፡ ይህን መንገድ ከተከተልኩ፡ ውሃ አገኛለሁ" አለ። ፈረሱም ምላሱ እስኪንጠለጠል ድረስ፡ በጥም ደረቀ፡ አፍንጫው ወደ ቀይ ተቀይሮ በአሸዋ እስኪጋገር ድረስ በጣም ክስል አለ። በዚያ የአሸዋ ማዕበል መካከል፡ በውኃ ጥም ከሰል እስኪመስል ድረስ፡ መሃረቡን ፊቱ ላይ አድርጎ ነበር። ፈረሱን እየመራ ሳለ ድንገት ዱካውን አገኘ። በፈረሱ ላይ በወጣ ጊዜ፡ የዱር እንሰሳት ዱካ አገኘና፡ "በእርግጥ ወደ ውሃ ይመራኛል፡" አለ። ስለዚህ ዘሎ ፈረሱ-ላይ ወጣና ዱካውን ተከትሎ መሄድ ጀመረ።

78 ፈረሱም ወደ ውሃ የሚወስደውን መንገድ እንደ ሆነ አወቀች። እግዚአብሔር ዲዳ ለሆኑት ለእንሰሳት በደመ ነፍስ እንዴት እንደሚመራቸው! ስለዚህም ዱካውን ተከተለች። በስተመጨረሻ፡ በትንሹ ወደ አንድ ጎን ዞረች፡ ከመንገድ ገለል አለች። ፈረሱ በዚያ መንገድ ለመዞር ፈልጋ ነበር፡ ኮይ ግን ሌላ ሀሳብ ነበረው። በደንብ በተረገጠበት በዋናው መንገድ ላይ ለመቀጠል ሞከረ፡ ያንን አቅጣጫ ያዘ ፈረሱ ግን ወደ ፊት አልሄድም አለች። በእግሩ ነካ አደረጋት፡ ጮኸች እና ወደ ሌላ አቅጣጫ ሄደች። እና ወደ ኋላዋ መዝለል ጀመረች። እሱን የማንሳት አቅም ግን አልነበራትም።

79 እናም ፈረሱን እስኪያደማት ድረስ፡ ውሃ ለመጠጣት በጣም ጓጉቶ፡ እንደገና በጫማው ብረት እሷን መውጋት ጀመረ። ፈረሱ እየደማች፡ እየተነቀተቀጠች፡ እስክትቆም ድረስ፡ ህይወቱን ማትረፍ ፈለገ። ወደ ታች ተመለከተ፡ አየም፡ ከእግሩ ስር ልትወድቅ ትንሽ ቀርቷታል **እንዲህ** እየተንቀጠቀጠች ነበር። ቁልቁል ተመለከታት፡ በጎኗ በኩል ደም አየ። ክርስቲያን ነበር። ፈረሱንም ተናገራት፡ እንዲህ አላት፡ "ብዙ ጊዜ የዱር እራዊት... ወይም፡ አውሬዎች ደመ ነፍስ እንዳላቸው ሰምቻለሁ። መንገድ ቀይረሽ የዞርሽኝበት ያንን ተራ መሳይ አቅጣጫ ወደ ውኃው መሄጃ አልመሰለኝም። ይህም ሰፊው መንገድ ወደ ውሃ ደጋግመው ወደሚሄዱበት

ቦታ የሚወሰድ አቅጣጫ ይመስላል፡ ይሁን እንጂ፡” “ይሄን ያህል ርቀት በታማኝነት ከተሸከምሽኝ፡ ደመ ነፍስሽ የሚልሽን እከተላለሁ፡” አላት።

80 አቤት፡ ስለ ክርስቶስ ያለኝ አሳብ ያ ነው! ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ በምልክት እና በውበት ያጌጠ ነው፡ ወደ ሕይወት የሚወስደው መንገድ ግን ጠባብ ነው። የሚያገኙት ጥቂቶች ናቸው። ይህም፡ በደመ ነፍስ አይደለም፡ ወደ ሕይወት ውሃ እንድትዞሩ የሚመራችሁ ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። እስከዚህ ርቀት ድረስ በሰላም እንዳደረሰኝ፡ አሰባለሁ፡ የቀረውን መንገድ እሄድበታለሁ።

81 ታሪኩን ለማጠቃለል ያህል፡ ግ—ግማሽ ማይል ያህል ሳይርቅ፡ እነሆ፡ በድንገት፡ ታማኟ ፈረሱ ወደ ትልቅ የውኃው ኩሬ ዘው ብላ ገባች። ፈረሷ ይህን አይነት ድርጊት በማድረጓ፡ ለ—ሚጋልባት ሰው ምን እየተናገረች እንዳለች ታውቃለች። እሱም ደረሰ። ወደ ፈረሱ አፍንጫ ላይ ውኃን መርጨት ጀመርኩ አለ። ታጠበ፡ ጮኸ እንዲሁም ኡኡ አለ፡ ድምጹን ከፍ አድርጎ ጮኸ። ጉሮሮውን በውኃ እያረጠበ፡ እንዲህ በማለት ጮኸ፡ “ተርፈናል! ተርፈናል! ተርፈናል!” ፈረሱም፡ እየጠጣች ትንቀጠቀጥ ነበር። በጫማው መውጊያ ምክንያት፡ የቆሰለውን፡ የደማውን ጎኗን ተመለከተ።

82 ወዲያውም፡ የሆነ ሰው… አንድ ሰው፡ “ከውኃው ውጣ” ሲለው ሰማ። አየም፡ በዚያም አንድ የተጎሳቆለ ካውቦይ ቆሞ ተመለከተ። ከውኃውም ወጣ። ከዚያም እሳት ሽተተኝ አለ፡ ዙሪያውን ተመለከተ፡ እና በዚያ ዙርያ የሰፈሩ ሰዎች አሉ። ሁሉም የዳሳሽ አለባበስ ለብሰው ነበር። ወርቅ አግኝተው፡ ፈረሶቻቸውን ይዘው ሲመለሱም ፈረሶቻቸውን ጭነው፡ ወደዚህ የውኃ ኩሬ መጥተው እረፍት እያደረጉ ነበር፡ ሁሉም ሰክረው ነበር።

83 እነርሱም ጥቂት የአጋዘን ስጋ እየጠበሱ ነበርና፡ አብሬአቸው በላሁ አለ። ከመካከላቸውም፡ አንደኛው “ጠጣ፡” አለው። እርሱም ሰለማንነቱ አጫወታቸው፡ ጃክ ኮይ እንደሚባል፡ የህንዶች አ—አሰጎብኚ እንደሆነ ነገራቸው። ስለዚህ፡ “እሺ፡ አሁን፡ ጠጣ” አለው።

እሱም፡ “አይ፡” “አልጠጣም፡” አለ።

84 ይህም ለሰዎቹ እንደመሳደብ ያህል ነበረ። እሱም አለው፡ “መጠጣችን መቀበል አለብህ!”

“አይ፡ መጠጥ አልጠጣም፡” አለ።

85 በድንገት ማሰሮውን ወረወረበትና፡ “ጠጣ!” አለው። ሁሉም፡ ሰክረው ነበር፡ እንግዲህ፡ ግማሽ ደርዘን ያህሉ ነበሩ።

እሱም አላቸው፡ “አመሰግናለሁ፡ ጓዶች።”

86 “ሥጋችን ለመብላት ከጣፈጠህ፡ ውስኪችን ለመጠጣት ይጣፍጣል፡” አሉት።

87 ሁኔታቸው ሁሉ ታውቃላችሁ፡ ሰክረው ነበር። እሱም፡ “አይ፡” አላቸው።

88 ካዝናውን ጠመንጃቸው ውስጥ ሰኩና፡ እንዲህ አሉት፡ “አሁን ትጠጣለህ እምቢ ብትል ዋ!”

89 እርሱም፡ “አይ። አይ፡ አልጠጣም፡” አላቸው። ጠመንጃውንም ደቀነበት። እሱም “አንድ አፍታ ብቻ” አለው። እሱም “መሞትን አልፈራም፡” አለ። “እኔ—

መሞትን አልፈራም፡” አለ። “መጀመሪያ ግን እኔ—ለምን እንደማልጠጣ፡ ታሪኬን ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡” አላቸው። “እኔ ኬንታኪያዊ ነኝ፡” አላቸው። እንዲህ አለ፡ “አንድ ቀን ጠዋት በትንሽ ጎጆ ቤታችን ውስጥ፡ እናቴ ሞት አፋፍ ተኝታ ሳለች፡ ወደ አልጋዋ አጠገብ ጠራችኝ፡ እና እንዲህ አለችኝ፡ ‘ጃክ፡ አባትህ የቁማር ካርታውን በእጁ እንደያዘ፡ ጠረጴዛው ላይ፡ በሰካር ሞተ።’ ‘አንተ ግን ጃክ፡ ምንም ቢመጣ እንኳን፡ ፈጽመህ እንዳትጠጣ’ አለችኝ።” እኔም፡ “እጆቼም በእናንቴ ግንባር ላይ ጫንኩ። ገና የአሰር-ዓመት-ታዳጊ ሆኜ፡ በፍጹም አንድም አልጠጣም በማለት፡ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ገባሁ።” ስለዚህ “ጠጥቼ አላውቅም፡” አላቸው። “አሁን ግን መግደል ከፈለጋችሁ፡ ግደሉኝ፡” አላቸው።

90 ሰካራሙም ጠመንጃውን አንስቶ ማሰሮውን እንደገና ዘረጋና፡ “ጠጣ ወይም እተኩሳለሁ፡” አለው! ያን ጊዜ ጠመንጃ ተተኮሰ ማሰሮውም ተሰበረ።

91 እነሆ አንድ የተጎሳቆለ ካውቦይ፡ ከገደሉ አጠገብ ቆሞ ነበር፡ እንባዎቹም በጉንጩ ላይ ይወርዱ ነበር። እንዲህም አለ፡ “ጃክ ሆይ፡ እኔም የመጣሁት ከኬንታኪ ነው። አንድ ቀን ለእናቴ እኔም ቃል ገባሁላት፡ ቢሆንም ቃሌን አፈረስኩ።” እንዲህም አለ፡ “እነዚህ ሰዎች እስኪሰክሩ ድረስ እየጠበቅኩ ነበር፡ እነዚህን ሁሉ፡ እንዲሁ ገድዬ፡ የያዙትን ወርቅ ለመውሰድ ተዘጋጅቼበት ነበር።” እንዲህም አለ፡ “እኔ ግን ሰካራም ሆንኩ እና ተሳሰቻለሁ። ቢሆንም፡” አለ፡ “የጠመንጃዬ ድምጽ በሰማይ ገደሎች ሲያስተጋባ፡ እናቴ እንደገና እንደማላደርገው ቃል መግባቴን ሰምታኛለች።” በዚያም፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ በዚያ የነበሩትን፡ ሰዎቹን በሙሉ ወደ ክርስቶስ መራቸው።

92 አያችሁ፡ ስለ ውሃ፡ ስለ መርካት አዲስ ነገር አለው። የእኔ ሃሳብ፡ ሲጠማችሁ ውኃ ስለመጠጣት ነው። ሲጠማችሁ እና ውሃው ላይ ስትደርሱ፡ የሆነ ነገር አለው።

93 አሁን፡ እርሱም እንዲህ ብሎናል፡ “ሰላሜን እተውላችኋለሁ። ሰላሜን እሰጥሃለሁ።” አለም እንደሚሰጣችሁ ሰላም ሳይሆን፡ እሱ እንደሚሰጣችሁ ሰላም ነው። የእርሱ ሰላም ጥማችንን ያረካል። ሰላምን የምንፈልግ ከሆነ፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም እንዳለን እውቀን በሚሰጠው ሰላም እንታደስ። ሰላምን-የሰጠን ጥማችንን የሚያረካ እርሱ ነው።

94 እርሱም የእውነት መብልና መጠጥ ነው ይላል ጥቅሱ። እዚህ ቁጥር 57 ላይ፡ “እውነተኛ መብል መጠጥ፡” የሚለውን ጥቅስ ላይ ምልክት አድርጌያለሁ። እዚህ ላይ የሚናገረውን አድምጡ።

> እነሆ **ሕያው አብ እንደ ላከኝ፡ እኔም** በአባቴ **ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝም፡ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።**

95 በሌላ አነጋገር፡ “አብ ላከኝ፡ እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ሁሉ ደግሞ በክርስቶስ መኖር አለበት።” ኦህ፡ ማይ፡ ይኸው፡ የጌታ እራት ማለት ይህ ነው። በክርስቶስ ስትኖሩ የምታገኙት እውነተኛው የጌታ እራት ይህ ነው።

96 አሁን፡ ሰውነታችን ሥጋዊ አካላችንን፡ ለማኖር፡ በየቀኑ ምግብ እና መጠጥ ያስፈልገዋል። በየቀኑ ካልተመገብን እና ካልጠጣን፡ ሰውነታችን ደካማ ይሆናል። በውስጣችን ምግብ እንድንወስድ የሚፈልግ ነገር አለ። የአንድ

ቀን ምግብ ለቀጣዩ ቀን አይቆይም። ሟች ሰውነታችሁን ለማጠናከር፡ በየቀኑ ምግብ መውሰድ አለባችሁ። መኖር ትችላላችሁ፡ ቢሆንም ትዳከማላችሁ። በሁለተኛው ቀን፡ እንዲሁ ትዳከማላችሁ። እና በሶስተኛው ቀን፡ በጣም ትዳከማላችሁ።

97 እንግዲህ፡ ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊው ዓለም የምናደርገው ያ ነው። አያችሁ፡ ዘወትር ከክርስቶስ ጋር መመገብ አለብን። በየቀኑ ከእሱ ጋር መነጋገር አለብን። በየቀኑ ሁሉን ነገር በእርሱ ዘንድ ማረም አለብን። ጳውሎስ "ዘወትር እሞታለሁ፡" ብሏል። አያችሁ? "ዘወትር፡ እሞታለሁ፡ እኔ ሕያው ብሆንም እንኳ፡ አሁን የምኖረው እኔ አይደለሁም በእኔ የሚኖረው ክርስቶስ ነው እንጂ።" ስለዚህ፡ ሥጋዊ ሰውነታችሁ በሕይወት ለማኖር በየቀኑ ምግብና መጠጥ ካስፈለገው፡ ለመኖር ይህ ካስፈለገው፡ እንግዲያውስ መንፈሳዊ ሰውነታችሁም ለማኖር፡ መንፈሳዊ መብል እና የጌታ እራት ያስፈልገዋል። አዎን። ኢየሱስ፡ "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" ብሏል። ስለዚህ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ዘወትር ማጥናት አለብን። አንዳንድ ሰዎች በጭራሽ አያጠኑትም። አንዳንድ ሰዎች በዓመት ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ ቢያነሱት ነው። እውነተኛ የሆነ፡ በእውነት በመንፈስ ጠንካራ የሆነ፡ እውነተኛው አማኝ፡ ግን፡ በየቀኑ መጽሃፍ ቅዱሱን ያነባል ከጌታ ጋርም ያወራል። ትክክል ነው። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] መሆንም አለበት። "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።"

98 ሌላው፡ ምግብ የምንመገብበት ምክንያት፡ ሰውነታችን በሽታን ለመቋቋም ለማጠናከር ነው። ምግብ ካልተመገባችሁ፡ እና ሰውነታችሁም እንዲዳከም ካደረጋችሁ፡ ለበሽታዎች የተጋለጠ ይሆናል። በሽታዎች ወደ ደም ውስጥ ይገባሉ፡ ከዚያም ይጨርሷችኋል። ደማችሁ ንጹህ እና ብርቱ ካልሆነ፡ እንግዲያውስ፡ ይህ ይሆንባችኋል፡ በሽታ ወደ ደም ስራችሁ ስተት ብሎ ይገባል። ስለዚህ የደም ስሮቻችሁን በትክክለኛው አቋም ለማቆየት ገንቢ ምግቦችን መመገብ አለባችሁ። ካልተመገባችሁ፡ የህመም አለርጂ ያጠቃችኋል። የብዙ ክርስቲያኖች ችግር ያ ነው።

99 ከችግኝ እንደወጣ ተክል ነው። ታውቃላችሁ አይደል፡ አንድን ተክል ከችግኝ ስታነሱት፡ እንደ ህጻን መንከባከብ አለባችሁ። የአየር ሁኔታውን አያውቀውም። የፀሐይ ብርሃንን እና ሌሎች ነገሮችን አያውቅም፡ ተሸፍኖ የተወለደ ነው። የብዙዎች ክርስቲያን-ተብዬዎች ችግርም ይህ ነው፡ የችግኝ ተክሎች ናቸው። ልክ ነው፡ ለብዙ አይነት ታህዋሲያን ተጋላጭ ናቸው! ታውቃላችሁ፡ መድሓኒት የሚረጭባቸው ብ—ብቸኛ... ብ—ብቸኛ ተክሎች፡ ለሰላሳ የሆኑት፡ ወይም ድቅል ተክሎች ብቻ ናቸው።

100 ታውቃላችሁ፡ አንድ የሄርፎር ከብት ወደ ማሳ ብትለቁት፡ በዚያም ረጅም ቀንድ ቢያበቅል፡ ኦርጂናል ዝርያ ስለሆነ ያበቀለው ቀንድ አይከብደውም። ብራንጉስ ወይም ሄሬፎርድ የተዳቀለ ዝርያ ብትወስዱ ግን፡ ለአይን የሚያምር ከብት ነው፡ በትክክል፡ ወፍራም እና ጤናማ ናቸው፡ ይሁን እንጂ ወደዚያ ብትለቋቸው፡ አይመለሱም። ይሞታሉ! እንክብካቤ ይፈልጋሉ። አያችሁ?

101 ዛሬ እየሆነ ያለው ይህ ነው፡ የተሻለ-አለባበስ የለበሱ ክርስቲያኖች፡ ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡ ብዙ—ትምህርት፣ ብዙ ስነ መለኮት

አላቸው፡ ነገር ግን ሁልጊዜ እንደ ህጻን እንክብካቤ ይፈልጋሉ፡ በመነጽራቸው ካላያችሁ በቀር አይን የላችሁም። እኛ የሚያስፈልገን በጌታ በኢየሱስ ደም የተወለዱ፡ ንጹሐን ክርስቲያኖች፡ ሕይወታቸውን ከቤተ ክርስቲያን ሰነ መለኮት ሳይሆን፡ ከእግዚአብሔር ቃል፡ ከክርስቶስ የጌታ እራት ጋር የሆኑ ናቸው። ቃሉ ወደ አማኝ ሲገባ፡ መንፈሳዊ አ—አካሉ ይገነባል። የችግኝ ማፍለያ ልጅ አይደለም!

102 ዛሬ አንድ አገልጋይ፡ በመገናኛ ብዙኃን ሲናገር፡ እንዲህ ሲል ሰምቼዋለሁ፡ እንዲህ አለ፡ ወደዚህ አገር በመጣ ጊዜ፡ ከባድ የሳይነስ ችግር ነበረበት፡ ስለሚያደርጉለት ቀዶ ሕክምና ሲያወሩ፡ **ይህን** እና **ያንን** እንደሚያደርጉ፡ እና ቀዶ ጥገና እንደሚያደርጉለት፡ ከሳይነስ ግላንዱ ከፊሉን ቆርጠው እንደሚያሰወግዱለት፡ ያም ፊቱ እንዲጎረጉድ ያደርግበታል፡ እና እንዲህ የመሳሰሉ ነገሮች ሲያወሩ ነበር። እርሱም በርሜል ሙሉ ክኒኖችን እንደወሰደ ተናገረ። እጅግ ብዙ ክኒኖች መውሰድ ነበረበት። ወደ አንድ ጥሩ ክርስቲያን ዶክተር ሲመጣ ግን፡ ዶክተሩ እንዲህ አለው፡ “ክኒናውን እና ቀዶ ጥገናውን እንተወው፡ እና የሳይነሱን በሽታ መቋቋም እንዲችል የሰውነት ግንባታ እንጀምር።” ይኸው ነው!

103 ሰዎች እንደ ቀድሞው የማይኖሩበት ጉዳይ ምንድን ነው? **ለዚህ** መርፌ **ለዚያም** መርፌ ስለምንጠቀም፡ እራሳችንን ለብዙ አይነት መድሐኒቶችን ስለምናጋልጥ ነው። ምን ያስከትላል? ለሰላሶች፡ ወፍራሞች፡ ልል፡ የማያምሩ እንድንሆን ያደርገናል። መቼም የጥንት ሰው... እና፡ እኛ እንደሆነ ለሁሉም ነገር አለርጂክ ነን። በዚህ ጊዜ የወባ-አለርጂ እና ሌሎች ነገሮች አሏቸው።

104 ወደ አፍሪካ ሄጄ ነበር፡ የወባ መከላከያ ክትባት ባልወሰድ። የወባ ትንኝ በእጄ ላይ ብታርፍ፡ ወባ እታመማለሁ። ድምጽ አያሰሙም፡ በጭራሽ አታውቋቸውም። ያርፉባችኋል፡ በላያችሁ ላይ ያርፋሉ፡ ያን ጊዜ፡ ትያዛላችሁ። በህይወት ከቆያችሁ፡ ለአስራ አምስት አመታት ያክል ትሸከሙታላችሁ። ከጊዜ በኋላ በዚያው ሰበብ ትሞታላችሁ። የአገሬው ተወላጆች በዚያ በትንሽ ጎጆአቸው ውስጥ፡ እርቃናቸው ሆነው፡ እግሮቻቸው በትንኝ ይሸፈናል። የወባ ትንኞች፡ ላያቸው ላይ ሰፍረውባቸው፡ በምንም አያስቸግሯቸውም። ለምን? በሽታን የመከላከል አቅም ገንብተዋል። ከእግዚአብሔር-የተሰጠ ክትባት አላቸው።

105 ዛሬ በሰዎች ላይ ያለው ችግር ይህ ነው። የቤተ ክርስቲያን ችግር ይሄ ነው። ብዙ የልጅ ክትባቶች እና ብዙ ሰው-ሰራሽ ሰነ መለኮቶች፡ ሙሉ በሙሉ ተርከፍክፎብናል። የሚያስፈልገን በጌታ በእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ክትባት ነው። ሰው በአገሪቱ ከሚዘዋወረው ወረርሺኝ እራሱን ለመጠበቅ፡ ከመንፈሳዊ ደዌ ለመከላከል እና ነፍሱን ለመገንባት ዘወትር በእንደዚህ ዓይነት መብል መኖር አለበት። እጅግ ብዙ ማስታወሻዎች ቀርተውኛል፡ ቢሆንም እዚህ ላይ ማቆም አለብኝ።

106 አሁን፡ ራሳችሁን አበርቱ፡ ራሳችሁን ለክትባት አዘጋጁ። መኖር ያለብን፡ በዚህ ነው፡ ሰ—ሰውነታችን ይህን ማግኘት አለበት። ካላገኘን ግን፡ ለብዙ አይነት በሽታዎች ተጋላጭ ነን። ስለ እግዚአብሔርም ቃል ግን፡ እምነን በጌታ እራት እንደተቀበልነው። “ጌታ ሆይ፡ ቃልህ እውነት ነው።”

107 “ቤተ ክርስቲያኗ ዳግም መወለድ የሊብህም ትላለች። ‘እጅ መጨባበጥ ዳግመኛ መወለድ ነው’ ይላሉ። ‘መረጨት፡’ ይላሉ። ሌላ ሌላ ነገሮችም ይላሉ፡ ‘አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ።’” መጽሐፍ ቅዱስ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ይላል። አያችሁ? እንግዲህ፡ እናንተም ከፈለጋችሁ በአርቴፊሻል መርፌዎቻችሁ ቀጥሉ፡ እራሳችሁን አርቴፊሻል ክርስቲያኖችን ታደርጋላችሁ። አያችሁ? ያ አያስፈልጋችሁም።

108 ከክርስቶስ በቀር፡ ሕይወት ሊኖራችሁ አይችልም። ቃሉስ ምን ያፈራል? ከእርሱ ጋር ስንመገብ፡ ዲያብሎስን ለመቃወም፡ መንፈሳዊ ሰውነታችንን ይገነባል፡ ያበረታታል።

109 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ይህ አንተ፡ ‘በቃሉ መመገብ’ የምትለው ነገር ምንድነው፡” ብላችኋልን?

110 አዎን፡ እርሱ ቃል ነው። “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃል ስጋ ሆነ በእኛም መካከል አደረ።” ሥጋውንም መብላት አለብን። ስለዚህ እርሱ ቃል ስለሆነ፡ ሰውነቱ ቃል ነው። በዮሐንስ ወንጌል 15 ላይ፡ “በእኔ ብትኖሩ፡ የጌታ እራቴም፡ ቃሌም፡ በእናንተ ቢኖር፡ የምትወዱትንም ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።” ይኸው። እውነት ነው። አያችሁ፡ የምትፈልገውን ጠይቅ!

111 ምን እያደረጋችሁ ነው? ሰውነታችሁን ታጠናክራላችሁ እንዲከተብላችሁ... አንድ ሰው መጥቶ፡ “ኑህ፡ ቤተ ክርስቲያናችን በእልልታ አታምንም።” አያችሁ፡ ገንብታችኋል። ምን? በእናንተ ዘንድ የጌታ እራት፡ ቃል አለ። እናንተም በዚያ ትከተባላችሁ። እርባና ቢስ ነገሮች ከበዙባችሁ፡ ምን ይባላል? ቃል የለውም፡ እንግዲያውስ ስሕተት መሁኑን እርግጠኛ ትሆናላችሁ። ምንም ያህል እውነት ቢመስልም ግድ የለኝም፡ ቃል ካልሆነ ተውት። በእውነት፡ ተውት። ምንም ቢጠቅም አይገደኝም፡ ከቃሉ ጋር መነጻጸር አለበት!

112 በጸሎት ውስጥ፡ ቆሜ ከሚክያስ ሰጠቅስ፡ ይኸውላችሁ፡ ይህ በእስራኤል ፊት፡ በእውነት ትክክል ይመስላል፡ ያቺ መሬትም የእነርሱ ነበረች። እነዚያ ወራሪዎች መጥተው ወስዷት በዚያም ቤቶቻቸው ገንብተውባት ነበር፡ እግዚአብሔርም ከሰጣቸው ምድር ከፊሉን ይዘውባቸው ነበር። ስለዚህ እነዚያ አራት መቶ ዕብራውያን ነቢያት ትክክል ይመስሉ ነበር። ታውቃላችሁ፡ ኢዮሣፍጥ ግን፡ የሆነ መንፈሳዊ ማንነት ነበረው፡ እንዲህም አለ፡ “ሌላ የለህምን? ”

113 አለውም፡ “አንድ ሌላ አለኝ፡ ቢሆንም፡” “እጠላዋለሁ። ክፉ ብቻ ይተነብይብኛልና፡” አለው።

“ሂድ እና አምጣው እርሱን ደግሞ እንሰማው፡” አለው።

114 ወደዚያ መጥቶም፡ አለው፡ “ሂድ፡ ሂድ ተከናወን፡ እስራኤል ግን እረኛ እንደሌላቸው በጎች ሲበተኑ አየሁ።” ያየውን ራእዩን ተናገረ።

115 አሁን፡ እውነት የትኛው ነው? አራት መቶዎቹ ትክክል ይመስላሉ። አራት መቶ የሰለጠኑ ሰዎች፡ “ሂድ፡ ጌታ ከአንተ ጋር ነው፡” አሉ። ሴዴቅያስ የሆነ ነገር ይ—ይ—ይዞ ነበር... ሴዴቅያስም ሁለት ትላልቅ የብረት ቀንዶች ሠራ።

እንዲህም አለ፡ “እነሆ በዚህም ወራሪዎቹን ከምድር ላይ ታሰወጣቸዋለህ።” ትክክል ስለመሆኑ እርግጠኛ ነበር። ትክክል ስለመሆኑ አውቋል። ቢሆንም፡ ይኸውላችሁ፡ ተሳስቶ ነበር።

116 እነሆም፡ ሚክያስ፡ በአራት መቶ ላይ ብቸኛ ነበር። እርሱም “ብትሄድ፡ እስራኤል ትበታተናለች፡ እረኛም አይኖራትም፡” አለው።

117 ሌሎቹም፡ “ሂድ፡ ጌታ ካንተ ጋር ነው!” አሁን፡ ቁሳዊ መሰረት በማድረግ፡ ልክ ነበሩ፡ መሬቱ የእስራኤል ነበረ። ይሁን እንጂ የጌታ ቃል አክዓብን አውግዞት ነበር፡ እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔር አንዴ ያወገዘውን እንዴት ይባርካል?

118 ዛሬም ያው ነው። አያችሁ? የጌታ እራት ቃል በሚኪያስ ዘንድ ነበረ። አሁን፡ ትክክለኛውን የጌታ እራት በመካፈል ከእግዚአብሔር ጋር ከተመገባችሁ፡ በእናንተ ዘንድ ያለው መንፈስ ከዚህ ቃል ጋር ባይስማማ፡ ከዲያብሎስ ጋር እንጂ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ እየተመገባችሁ አይደላችሁም። እነርሱም እጅግ ያስመስሉታል! መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ “በመጨረሻ ዘመን ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስታሉ። ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንጂ፡ ቃሌ ግን አያልፍም።” እናም... ጳውሎስ፡ በገላትያ 1:8 እንዲህ ከተናገረ፡ “መልአክ ከሰማይ ወርዶ አስቀድማችሁ ከሰማችሁት ወንጌል የሚለይ ቢሰብካችሁ፡ የተረገመ ይሁን።” መልአክም ቢሆን! በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን በነበሩ ሰዎች ቅዱስ ማርቲን፣ ኢራኔዎስ፣ እና ቅዱሳን ሰዎች፡ ዲያብሎስ እንደ ብርሃን መልአክ ይገለጥ ነበር። ሲገለጥም፡ አስተውሉ፡ በትንሹ ከቃሉ ይዛነፋል።

119 ሔዋንን የብርሃን መልአክ መስሎ፡ ተገለጠላትና፡ “በእውነቱ፡ ጌታ **ይህን** ተናግሯል፡ ጌታ **ይህን** ብሏል” አላት፡ ሁሌ ግን ባለቀ ሰዓት ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ይቃረናል። ዛሬም የተሳሳተ የጌታ እራት የሚደረገው በዚህ ነው። ሰዎች ቃሉን ሳይታዘዙ፡ በእግዚአብሔር ፊት እየጸለይኩ ነው ሲሉ፡ ይህ የውሸት ጌታ እራት ነው።

120 “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡ የምትወዱትን ጠይቁ፡” አያችሁ፡ “ይሆንላችኋል።” አሁን፡ እንዴ ታዛችሁት፡ በሚቀጥለው የምትለቁት አይደለም። “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፡” **ቢኖሩ** ማለት፡ “አንድ ሰፍራ ላይ፡ ማረፍ፡” ማለት ነው። አዎን፡ የኃጢአት በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ክትባት ነ—ነው።

121 አሁን፡ በመዝጊያ ላይ ወደ ጌታ እራት ሰርዓት ከማለፋችን በፊት፡ ይህን አንድ ቃል መናገር እፈልጋለሁ። የጌታ ደም እና ስጋው፡ ከእምነት ጋር በአንድነት ሲደመሩ፡ ሰጋው እና ደሙ ማለት፡ ቃሉ እና መንፈሱ ናቸው፡ ከእምነት ጋር ሲደመሩ፡ ውጤቱ የዘለአለም ህይወት ይሆናል። “ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።” ይኸው ነው። ይህ ምንድነው? የጌታ እራት ይህ ነው። ቃሉ እና መንፈሱ፡ ይህ ህይወት በደሙ ውሰጥ አለ፡ በጌታ ዘንድ ባለን እምነት፡ ቃሉ እና መንፈሱ ሲደመሩ ሁለቱ ዘለአለማዊ ህይወት ናቸው።

122 እና በማንኛውም ደቂቃ፡ አንዳች ነገር ሊከሰት እንደሚችል፡ መጨረሻው ሲቃረብ፡ እና ከጌታ ምጽአት፡ የራቅን አለመሆናችንን ሰመለከት ጸሎቴ ይህ ነው፡-

ጌታ ሆይ፡ እንግዲህ በእግዚአብሔር ልጅ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ አቤቱ ቃሉን፡ ሰይፉን ይዤ፡ ባለኝ እምነት እያወዛወዝኩት፡ ቃሉን በመመገብ ኢየሱስን እንዳይ፡ የአጋንንት ኃይላትን በሙሉ፡ ቆራርጬ እንዳልፍ እርዳኝ።

123 ቃሉን መመገብ። “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ውስጥ ቢኖር፡ የፈለጋችሁትን ጠይቁኝ ይሆንላችኋል።” እንዴት ያምራል! ከቃሉ ጋር እና ከመንፈሱ ጋር፡ አንድ ላይ በእምነት የምናወዛውዝበት ትክክለኛውን የጌታ እራት ይህ ነው፡ “የምትፈልጉትን ጠይቁ፡ ይሆንላችኋል።” እንጸልይ።

124 ቸር እና ክቡር ቅዱስ አባት፣ እግዚአብሔር፣ ታላቁ **እኔ ነኝ**፣ የአብራሃሙ ኤልሻዳይ ሆይ። አምላክ ሆይ፣ ከጌታ ዘንድ ይህ ታላቅ የጌታ እራት ከዘላለማዊ ሕይወት ጋር ምንኛ እኩል ነው፡ እንዴት ያለ የትዕቢት ክትባት፡ እንዴት ያለ የአለማመን ክትባት፡ እንዴት ያለ የዓለም ኃጢአት ክትባት ነው! ለሰማዩ አባታችን ካለን መለኮታዊ ፍቅር ጋር፡ የጌታ እራት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ደግሞ ወደዚህ ገበታ የመቅረብ ድፍረት አለን። ጌታ ሆይ፣ ለእያንዳንዳችን በዚህ ምሽት ይህን የመቅረብ ድፍረት፡ በመንፈስ እንድትሰጠን፡ እንጸልያለን። ይቅር በለን። መንፈሳዊ ሰውነታችን እንዲያድግ እንፈልጋለን። ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት የመቀላቀል ፍላጎት የለንም። መንፈሳዊ አካልን መገንባት እንፈልጋለን፣ ስለዚህም የኃጢአት ክትባት ይሁንልን፣ ከአሁን በኋላ ክፉ የማድረግ ፍላጎት እስከማኖረን ድረስ ይሁንልን፣ መንፈስ ቅዱስም የገዛ ቃሉንና ከንፈራችንን በመጠቀም፡ በዚያ ቀን እንደ ተባለ ፍሬሽ የሆነውን ይናገረን፡ ምክንያቱም በጌታ በኢየሱስ የነበረው ያው መንፈስ ነው። አንተ አባት ሆይ፡ ይህንን እንድትሰጠን፡ እጸልያለሁ።

125 ጊዜው እያለቀ ነው። የመጨረሻው ሰው የሚድነው፡ መቼ እንደሚሆን፡ አናውቅም። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ ግን፡ አንተን እንደ አዳኛቸው ያላወቁህ እዚህ ካሉ፡ ወደ ጥምቀት ውሃው ሲገቡ አቤቱ አንተን ያግኙ፡ እንደመታሰቢያ፡ የአማኞች የታሪኩን አካል መሆናቸውን ማመናቸውን እንዲታመኑ ታሪኩም የናዝሬቱ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም እንደ ተወለደ፡ በጴንጤናዊው ጲላጦስም ተሰቅሎ፡ እንደተገደለ፡ በእግዚአብሔርም በሦስተኛው ቀን ተነሥቶ፡ ዛሬ ማታ፡ በግርማው ቀኝ ሆኖ፡ ዘወትር ሲያማልድ በህይወት እንደሚኖር ነው።

126 ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ትእዛዛትን፡ የሚያከብር ያው ሰው፡ “ንስሐ ግቡ፡ ለኃጢአታችሁም ስርየት፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። እንድንበት ዘንድ የሚገባ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።” አምላክ ሆይ፡ ሰዎች የዚህን ቅንነት፡ እና የቃሉ ጽናት ይዩ፡ “ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር ትድኑበት ዘንድ የሚገባችሁ ለሰዎች የተሰጠ ስም፡ ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።” ስለዚህ ሐዋርያው፡ “ንስሓ ግቡ፡ ለኃጢአታችሁም ስርየት እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክሰርቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታም ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው፡ በሁሉም ዘመናት ላሉ ሁሉ ነውና።” ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ብዙ ጥሪ ይሁንልን።

127 በተጨማሪም፡ በጌታችን፡ “አባቴ ካልሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል ማንም የለም፡ አብም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ።” ከሌላው ግን፡ ሌላው፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ድምፅ ቢናገር፡

ወዲያው በጎቹ ያውቁታል። አምላክ ሆይ! ድምፅህ ከሆነ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ፡ በውስጡ የሚናገረው ነገር፡ በግ የሆነው ሁሉ ይሰማዋል፡ የበግ መብል ነውና። በልተዋልና። አብ ምን አይነት ምግብ እንደሚመገብ ያውቃሉ። “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።” ጌታ ሆይ፡ ብዙዎች አይተው እንዲረዱ፡ እና ዛሬ ማታ ወደ አንተ እንዲመጡ፡ ሰጠን።

128 መንፈስ ቅዱስ ያልተቀበሉ፡ ሌላ ጊዜ አይጠብቁ። ሌላኛው ጊዜ እጅግ ሊረፍድባቸው ይችላል። እዚህ ላይገኙም ይችላሉና።

129 አቤቱ፡ አባት ሆይ፡ አሁን የተቆረሰው አካልህ ምሳሌ የሆነውን ምልክት ለመቀበል፡ በገበታው ዙሪያ እንደተሰበሰብን፡ በመካከላችን ኃጢአት ቢኖር፡ ጌታ ሆይ፡ ይቅር እንድትለን እንጸልያለን። “በአንድ ሰትሰበሰቡ፡ እርስ በርስ ተጠባበቁ፡” ብለኸናልና። እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ ጉባኤ ውስጥ፡ በየትኛውም ቦታ ኃጢአት ካለ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያንን ሰው፡ ወይ ያቺን ሴት፡ ወጣት ወይም ልጃ ገረድ ከኃጢአት እንዲለያቸው እጸልያለሁ። አባት ሆይ፡ ከጥርጣሬ፡ ከኃጢአት፡ ከእምነት ማነስ፡ ከሁሉም ነገር እንድታርቀኝ፡ ለራሴ እለምንሃለሁ። ማንኛውም... አለማመን ሁሉ ኃጢአት እንደሆነ እናውቃለን። ብቸኛው ኃጢአት እሱ ነው። “ያላመነ ግን ከወዲሁ ተፈርዶበታል።” ኃጢአት አንድ ብቻ ናት፡ ያውም የእግዚአብሄርን ቃል አለማመን። በእኔም፡ አባት ሆይ፡ አለማመን ከተገኘብኝ፡ ብዙ አለብኝና፡ አምላክ ሆይ፡ ማረኝ፡ ይቅር እንድትለኝ እጸልያለሁ። ዛሬ ምሽት የሰጠኸኝን ጉባኤዬን ይቅር በላቸው፡ እና በቃልህ መግባቸው። አሰበን።

130 እናም እነዚህን ትንንሽ የሰውነቱ ቁርስራሽ መታሰቢያዎችን ከሞት ከተነሣው ለዘለአለምም በመካከላችን ከሚኖረው ሰንቀበል፡ ጌታ ሆይ፡ አቤቱ የጌታ እራት ከእርሱ ዘንድ መቀበል ይሁንልን፡ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ መመገብ ነው። አሰበን፡ አባት ሆይ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

131 አሁን፡ ለእናንተ ለምትሄዱ እና የአስራ-አምስት ደቂቃዋ የጌታ እራት አገልግሎት መቆየት ለማትችሉ... የጌታ እራት የምንወሰድ፡ ብዙዎች አይደለንም። ዝግ የጌታ እራት አናደርግም። ለሁሉም ክርስቲያን አማኝ ፍጹም የተቻለ ነው። እግዚአብሔር በባፕቲስት እና በሜቶዲስት እና በመሳሰሉት መካከል፡ የተሰመረ ድንበር የለውም። በአንድ መንፈስ፡ ሁላችንም፡ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ነን። በመካከላችን እንግዳ ካለ፡ እንዳች ነገር አላውቅም፡ ማን የማን አባል እንደሆነ እና እንዳልሆነ አላውቅም። አስታውሱ፡ የየትኛው ቤተ ክርስቲያን አባል ብትሆኑ፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። በመሰረቱም፡ ቤተ ክርስቲያን አንድ ናት፡ እሷም የምትቀላቀሉባት ሳትሆን፡ የምትወለዱባት ናት። በትክክል። እናንተም ወደዚህ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የተወለዳችሁ ናችሁ። ዛሬ ማታም ክርስቶስን እንድትቀበሉት፡ ከእርሱ ጋር ለመመገብ የተቆረሰውን አካሉን ሰናሰብ፡ እና እነዚህን የምንቀበላቸውን፡ የፋሲካውን ቁርስራሾችን ሰንቀበል፡ እግዚአብሔር ልባችንን እና ሳሊናችንን በደሙ ይረጭን።

132 በመቀጠል የጌታ እራቱን ያመጡታል፡ እኛም ከአንደኛ ቆሮንጦስ፡ 12ኛው ምዕራፍ እናነባለን። ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ የጌታ እራት እንወስዳለን፡ እግዚአብሔርም አብዝቶ እንደሚባርካችሁ እናምናለን። ይህን እንዳነበብነው፡

ወይም ከማንበባችን በፊት፡ መውጣት ካለባችሁ፡ መልካም፡ በጸጥታ መውጣት ትችላላችሁ። እንደገና ረቡዕ ምሽት፡ እሁድ ጥዋት እና እሁድ ምሽት ኢብራችሁን ሁኑ። ከእኛ ጋር ህብረት ለማድረግ መቆየት ከቻላችሁ፡ ይህን በመቻላችሁ በጣም ደስ ይለናል። ወዲያውኑ ከዚያ በኋላ፡ በጌታ ዘንድ... የጥምቀት ስርዓት ይፈጸማል፡ ምናልባት ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ይደረጋል፡ በዛም ከሃያ ደቂቃ በኋላ፡ ይመስለኛል። አንደኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች፡ 11ኛው ምዕራፍ፡ 23ኛው ቁጥር።

**... ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፡ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት... እንጀራን አንሥቶ፥**

**አመሰገነ፡ ቆርሶም፡... እንካችሁ፡ ብሉ፡ አላቸው፥ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን፡ ሥጋዬ ነው፥ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።**

**እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፡ ከጠጣበት በኋላም፡** ይህ ጽዋ **በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፥ በጠጣችሁ**ት **ጊዜ ሁሉ፡ ይህን ለመታሰቢያዬ፡ አድርጉት፡ አለ።**

**ይህን እንጀራ** በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ **ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ፡ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ**ና።

**ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ** ያልበላ... **ስለዚህ ሳይገባው፡ ይህን እንጀራ የበላ፡ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ፡ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት።**

**ሰው ግን ራሱን ይፈትን፡ እንዲሁም** ከ**እንጀራው ይብላ፡** ከ**ጽዋውም ይጠጣ።**

**ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ፡ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ፡ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና።**

**ስለዚህ በእናንተ ዘንድ** የደከሙና የታመሙ **ብዙዎች አሉ፡... አያሌዎችም አንቀላፍተዋል።**

**ራሳችንን** ብንመረምር **ግን፡ ባልተፈረደብንም ነበር።**

**ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ፡ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን፡ በጌታ እንገሠጻለን።**

**ስለዚህ፡ ወንድሞቼ ሆይ፡ ለመብላት በተሰበሰባችሁ ጊዜ፡ እርስ** በርሳችሁ **ተጠባበቁ።**

133 አሁን፡ ለአፍታ የጸጥታ ጸሎት ለእያንዳንዳችን፡ እኔ ለእናንተ ስጸልይ ለእኔ ጸልዩልኝ። [ወንድም ብራንሃም በቀስታ ጸለየ—አርታዒ።]... ? ...

ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ፡ በእነዚህን ልመናዎች አሰባቸው። የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

134 እነዚህ ትንንሽ ቁርስራሾች ያለ ቅባት፡ ያለ ቅመም፡ ወይም ያለ ምንም ነገር የተዘጋጁ ህብስቶች ናቸው፡ ይህም የጌታን ስጋ ተምሣሌት ነው። የተቆራረሰ ነው እንጂ፡ ክብ አይደለም። ይህም ስለ እኛ የተቆራረሰውን የአካሉ ምሳሌ ነው። ለሚበላውም ሁሉ እግዚአብሔር በረከቱን ይሰጣቸው። እንግዲህ፡ ይህ የስጋው ተምሣሌት ብቻ ነው እንጂ፡ ስጋው አይደለም። ህብስቱን ከማዘጋጀት በቀር፡ ሌላ የመሥራት ሥልጣን የለኝም፡ ሌላም ማንም የለም። እግዚአብሔር ብቻውን። እሱ የነገረን ይህን እንጀራ በልተን ይህን የወይን ጽዋ እንድንጠጣ ነው። አሁን እንገታችንን እናጎንበስ።

135 እኛ ባሪያዎቹ የሆንን፡ ቅዱስ አምላክ ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይህንን ህብስት ስንቀበል፡ ጌታችን እንደተሰቀለ፡ እናስብ ዘንድ፡ ለዓላማው ቀድሰው፥ ስጋውም፡ ቅዱስ እና ድንቅ ሆኖ ሳለ፡ ስለ እኛ፡ በመግረፊያ እና ከእሾህ ጋር እንዲሁም ከሚስማር ጋር ተጣበቀ፡ ይህም የዘላለም ሕይወትን የሚሰጠን መንፈስ ከስጋው ይወጣልን ዘንድ ነው። እኛም፡ ጌታ ሆይ፡ ይህን ስንበላ፡ እስራኤል አርባ አመት በምድረ በዳ በመካከላቸው አንድም ሳይጎሳቆል እንደተጓዙ፡ አንድም ደካማ እንዳልነበራቸው፡ አቤቱ ለእኛም የጸጋ ጉዞ አድርግልን። እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፡ ይህን ህብስት፡ የቂጣ ህብስት፡ ለታሰበበት ዓላማ እንድታደርግልን ስንጸልይ፡ አሰበን። በኢየሱስ ስም። ኣሜን።

136 ደሙ፡ የአዲስ ኪዳን ጽዋ። መዝሙሩ ትዝ አለኝ፥

ያንን ምንጭ ካየው በእምነት
ከሚፈሰው ቁስል የሚወርድ፡
የመቤዠት ፍቅሩ መዝሙሬ ሆኗል፡
እስክሞት ድረስም ይሆናል።

137 ይህን ደም ባየሁ ቁጥር፡ ወይኑ፡ የወይኑ ደም፡ ከጌታ ከኢየሱስ ሥጋ የወጣውን ደም ተምሣሌት እንደሆነ አውቃለሁ። ይህን የሚቀበል ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይኑረው፡ ደዌ ከአካላቸው፡ ድካምና ጉስቁልና፡ እሰራት ሁሉ ይውጣ፡ (በልዩ ልዩ አይነት) የያዛቸው ዲባሎስ ይልቀቃቸው፡ ታላቅ ጥንካሬ እና ጤና እና የዘላለም ሕይወት ይኑራቸው፡ በዚህ የምንኖርበት ክፉና አመንዝራ ትውልድ ፊት ብርሃናቸውን ያበሩ ዘንድ፡ እግዚአብሔርን ለማክበር ይሁንላቸው።

138 የሰማይ አባት ሆይ፡ የወይኑን ፍሬ በፊትህ እናቀርባለን። የልጅህን፡ የኢየሱስን ደም ተምሣሌት ይሆን ዘንድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ቀድሰው፡ ከእርሱም ይህ ሆነልን፡ “ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።” ጌታ ሆይ፡ ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ፡ አስፈላጊ የሆነውን ጥንካሬ እና ጤና አግኝተን፡ አንተን ልናገለግልህ፡ ወደምንፈልግበት፡ እኛን ወደምትጠራንበት ቦታ አንተን ለማገልገል መሄድ እንድንችል አሰበን፡ የዘላለም ህይወት ወደ እኛ ይምጣ። በእነዚህ በረከቶች አሰበን፡ እያልን በኢየሱስ ስም፡ እንጸልያለን። ኣሜን።

62-0204 የጌታ እራት
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2025 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org